# ምዕራፍ አራት

## የእግዚአብሔር ባርያ ( አገልጋይ ) መሆን አያስፈልገንም

ተአምረ ማርያም የተባለውን መጽሐፍ ከማንበብ አታስታጉሉ አባቶቻችን አውግዘዋልና እንዲያውም ቅዱስ ቁርባንን መቀበል ያልቻለ እንኳ ሰው ቢኖር ተአምረ ማርያምን አንብቦ ወይም ሲነበብ ሰምቶ ወደ ቤቱ ከሄደ የጌታን ሥጋና ደም እንደተቀበለ ይቆጠርለታል ስለሚባል፣ በርካታው የቤተክርስቲናችን ምዕመን የቅዳሴውን ማለቅ በጉጉት እየናፈቀ ተአምሯ ነው የሚባለውን መጽሐፍ ሲነበብ ለመስማት ይቻኩላል::

አባ ሚካኤል አባ ገብርኤል የምንባል እኛ ተአምሯን ሳይሰማ የሚሄድን ሰው አውግዘናል በሚል ግዝት የሚከፈተው ይህ ተአምረ ማርያም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ያደረገችው ተአምር ይህ ነው:: በማለት ይጀምርና ምንም እንኳ እንደተጻፈ በውል ባልተረዳው አንባቢ አማካኝነት ተነብቦ « የሰማነውን በልቦናችን ያሳድርብን » በምትለው ጎጋዊ ዜማ ያዳምጥ የነበረውን ሕዝብ አመኔታ ይቀበሉና ዞረው በማሳለም ይሸኙታል::

አንባቢውም ሆነ ራሱ መጽሐፉ ሲጀምር በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ቢልም ከማደናገሪያነት ያላለፈው ይህ አባባላቸው በመንፈስ እግዚአብሔር ቢመረምረው ድብቁ የጸሐፊዎችም ሆነ የመጽሐፉ ዓላማ ቁልጭ ብሎ ይታየዋል::

እመቤታችን እንዲህ ያለ ተአምር ሠራች ሲለን የነበረው ይህ የተአምር መጽሐፍ በጌታችን እናት ስም ሽፋን ያገኘውን የምዕመናን ልብ ክፉ ዘርን በመዝራት ከእግዚአብሔር ጋር በማጣላት ዓቢይ ተልዕኮውንና ግብሩን ስርዋጽ በማስገባት ይተገብራል::

በርግጥ አንባቢውም ሆነ አስነባቢው የተነበበው ሆነ የተጻፈው ምን ይላል ከማለት ይልቅ ሁል ጊዜ በሚዜም የማስፈራሪያ ዜማ ይህን የተአምሯን መጽሐፍ የጻፈ ያጻፈ ያነበበ ያስነበበ የደገሰ ያስደገሰ እውነት እላችኋለሁ ዋጋውን አያጣም ስለሚሉ በመስማት ሆነ በማሰማት ላይ ያሉት ዋጋ ያስገኛል የተባለውን የመስማት ወይም የማሰማት ግዴታ ለመወጣት ከመታገል በስተቀር ስለመልእክቱ ትርጓሜ ወይም ምንነት ልብ የሚሉት አይደሉም ::

ይህም ይታወቅ ዘንድ በዚሁ በተአምረ ማርያም መጽሐፍ ላይ ዮሐንስ አፈወርቅ የተባለው ሊቅ የአንዲት ሴትን ኃፍረተ ሥጋ ( የሴቱ ብልት ) ጌታችን የተወለደበት በማለት በሳመው ጊዜ እመቤታችን ደስ ብሏት ተገለጠችና ስሙን «አፈ ወርቅ» በማለት ሰየመችው የሚለውን የእመቤታችን ተአምር ነው በማለት ተቀብለውት ይገኛል።

የሴት ብልት ( ኃፍረተ ሥጋ ) አሳፋሪ ነው ማለታችን ሳይሆን ዛሬ ሰለጠን በሚሉት ዓለማት እንደሚገኙት ስድ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ባለሙያዎች ሰዎች እንደ ዮሐንስ አፈወርቅ የሴትን ብልት « ጌታችን የተወለደበት ነውና » እያሉ ይህን ጸያፍ ባሕል መንፈሳዊ ሽፋን በመስጠት ለማስፋፋት መናፍስት በሃገራችን ምን ያህል ጥረት እንዳደረጉ ለማሳየት ነው። ( ተአም 48 ÷ 1 - 27 )

ተአምረ ማርያም የተባለው ይህ መጽሐፍ እመቤታችን እንዲህ አደረገች በረከቷ በእኛ ይደርብን ሲል ቆይቶ ሊል የፈለገውን ዋና ዓላማውን እንዲህ በማለት አስፍሮታል። መቼም መጽሐፉ የተነሳበት ዓላማ በብዙ ነገር ራሱን ለመሸፈን ቢጥርም ሰይጣናዊ እንደሆነ ነቢይ የማያስፈልገው ሕልም ፈቺ የማያሻው ሐቅ ነው።

በሃገራችን ስለአስመሳዮች የሚተረት ተረት አለ። የበጎችን ቆዳ ለብሶ በበጎች መካከልም ተደባልቆ ገበያ የወጣ አንድ ውሻ በግ ገዢዎች የበጎችን ጀርባ እየነካኩ ሊገዙ የሚፈልጉትን ዓይነት ሲያማርጡ በድንገት እዚያ በበግ ቆዳ ራሱን ሰውሮ ከነበረው ውሻ ላይ ይደርሳሉ ። ገዢዎችም እጃቸውን በጀርባው ላይ በጫኑ ጊዜ እውነተኛ የውሻነቱ ባሕርይ ተገልጦ እጃቸውን ለመንከስ አፉን እንደከፈተ » ይነገራል።

በቤተክርስቲያናችንም ዘመንን፣ መቅደሱን፣ ሥርዓታችንን ብዛታችንን፣ የአሰፋፈር ስፋታችንን ፣ የመጻሕፍቶቻችን ቋንቋ ለምዕመኑ ባዕድ መሆንን ተገን በማድረግ የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ በመገዳደር መልኩ ሲጽፉ ሲያስተምሩና ሲሰብኩ የነበሩት የቤተክርስቲያናችን ዕዳ ምክንያቶች የሆኑት እነዚህ ሰዎች ዛሬ በመንፈስ እግዚአብሔር አማካኝነት ጀርባቸው ሲዳሰስ እንደ አስመሳዩ ውሻ እውነተኛ ባሕርያቸው እየተገለጠ መጥቷል።

በዚህ በተአምረ ማርያምም ይህኑ የሚያስረግጠው ድብቅ አላማቸው እንዲህ ይነበባል።

አእኃውየ ኃጥአን እለ ከማየ እም ይእዜሰ ኢንኅሥሥ
ከዊነ አግብርተ እግዚአብሔር በፈጽሞ ሕግጋት ፲ቱ ወ፮ቱ
እስመ ውእቱ መጠወነ ኪያሃ... ወበእንተዝ እብለክሙ
ንቅድም ወንትባደር ከዊነ አግብርት ለማርያም እምነ
ወእግዝእትነ ... ወይእቲ ማርያም ... ትሬስየነ ንጹሐነ
በደማ ዘተክዕወ እምገቦ ወልዳ

*ትርጉም*:-

እንደኔ ያላችሁ ኃጥአን ወንድሞቼ ሆይ እንግዲህስ ወዲህ 16ቱን የሕግ ትዕዛዛት በመፈጸም የእግዚአብሔር ባሪያዎች ለመሆን እንሻ እርሱ እርሷን ሰጥቶናልና ... ስለዚህ እላችኋለሁ የእናታችንና የእመቤታችን የማርያም ባሪያዎች ለመሆነ እንሽቀዳደም ... ይህችውም ማርያም ከልጇ ጉን በፈሰሰው ደሟ ንጹሐን ታደርገናለችና:: ይላል /ተአምር፣ 12 ቁጥር 52 - 54/

**ይህ ጽሑፍ ሲመዘን**

1. **ከእንግዲህ ወዲህ** :-

ይህ ሐረግ እነርሱና ( ጸሐፊዎቹ ማለት ነው ) እየመሩት ያለው ሕዝብ የደረሰበትን ሁኔታ ለተሰወረው ዓላማቸው ብቁ መሆኑን የተረዱበት ጊዜ ላይ መድረሳቸውን የሚያሳይ ነው::

የሕዝቡን ኅሊና በቀናት፣ በመላእክት ፣ቅዱሳን በሚሏቸው ሰዎች ልደት ፣ሞት ፣ ፍልሰት ወ.ዘ.ተ በሚባሉት ምክንያት ሥርየተ ኃጢአት አለ በማለት ከክርስትና መስመር ካወጡት በኋላ « ከእንግዲህ ወዲህ» ወደ ፍጻሜ ደርሰናል አይነት ስሜትን የሚጭር መንደርደሪያ ነው ::

መጽሐፉ በወንጀል ታሪኮች የተሞላ ተረት እንደሆነ በርካታ ድርሰቶቻቸውን አቅርበን ማስረዳት ይቻለናል:: ጸሐፊዎቹ በፈለጉት ዓይነት የድርሰት የልብ ወለድ አጻጻፍ ዘይቤ ሕዝቡን ከኋላቸው ካሰለፉ በኋላ ወደፈለጉት ጉዳይ ለማስገባት አመቺ ሁኔታ ላይ እንዳደረሱት የቀረን ይህ ብቻ ነው ዓይነት ስላቅ ጽፈዋል::

አስቀድመው ወንጀልን ሲጽፉ ተቃውሞ ያላገኛቸው የድርሰቱ ባለቤቶች አሁን ብርቅየ ናፍቆታቸውን ለመግለጥ አመቺ ሁኔታ ላይ ነን ሲሉ ከእንግዲህ ወዲህ ብለዋል፡

## 2. ፲ ወ ፯ ቱ ቃላተ ወንጌል መጠበቅ አያስፈልገንም

ዋናውና የተጠበቀው የሚፈለገውም የመናፍቃኑ ዓላማ ይህ ነበር ፡፡ እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ጸጋ በክርስቶስ ኢየሱስ በተደረገ ቤዛነት በማመን ደህንነታቸውን ካገኙ በኋላ ሕገ እግዚአብሔርን በተሰጣቸው የመንፈስ ጸጋ እየጠበቁ የብርሃን ልጅነታቸውን ለዚህ ዓለም በመግለጥ በሕይወታቸው ሁሉ ምሥክር በመሆን እግዚአብሔርን አክብረውና አስከብረው ያልፉዘንድ ፈቃደ እግዚአብሔር መሆኑ ጌታችን የመጣበትን ሥራ ፈጽሞ ለመሄድ ጥቂት ቀናት በቀሩት ጊዜ ደቀመዛሙርቱን ሰብስቦ « ብትወዱኝስ ትዕዛዜን ጠብቁ » ባለው ተገልጧል፡፡

እንዲያውም ጌታችን ስለዚህ ነገር በአጽንኦት ሲናገር « ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው... ( የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እንዳርጋለን » በማለት ለሕጉ ለትዕዛዙ ትኩረትን ሰጥቶአል፡፡ (ዮሐ 14 :11 - 23 )

አስቀድመን እንዳልነው ከዚህ ከእግዚአብሔር ምህረትና ጸጋ ምዕመናንን ካወጡ በኋላ አሁን ደግሞ ያለ ፍርሃት በግልጥ « ትዕዛዙን መጠበቅ አያስፈልገንም » በማለት በዓውደ ምሕረቱ ላይ ሲናገሩ አሜን ያላላቸውን ሰው ጸሎት በሚመስል ርግማን « አሜን ያላሉትን አሜን አሰኝልን » በማለት አሜን እያሰኙ ኖረዋል፡፡

ለምን እንዲህ በድፍረት የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ አለመጠበቅ ወደዱ? ብንል ጌታችን በዮሐ 14፡ 29 እንደገለጠው « የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም » እንዳለው መሆኑ ይገልጥልናል፡፡

ይህን በተጨባጭ ለማስረዳት የገድል የድርሳንና የተአምር ጸሐፊዎች እንደገለጡት እነርሱ ጻድቃን ሰማዕታት እያሉ የሚጠሩአቸው ሰዎች ከጌታችን

ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ይልቅ ጸሐፊዎቹ እመቤታችን እያሉ ለሚገልጧት ፍቅር አክብሮት ምሥጋና ውዳሴ አምልኮ ይሰጡ እንደነበር በውዳሴ ማርያም ትርጓሜ እንዲህ ይነበባል፡፡ « ቅዱስ ኤፍሬም የተባለው ሰው (የውዳሴ ማርያሙ ጸሐፊ ያሉት) ሲመጸውት በሥላሴ ስም በመላእክት በሰማዕታት ስም አይመጸውትም ነበር፡፡ ለምን ቢሉ ... እመቤታችንን ከመውደዱ የተነሣ እመቤቴ ምሥጋናዋ እንደ ሰማይ ኮከብ እንደ ባሕር አሸዋ በዝቶልኝ እንደ ልብስ ለብሸው እንደ ምግብ ተመግቤው ጠግቤው እያለ ይመኝ ነበር » ብለው የሰውየውን ቅዱስነት አስፍረዋል፡፡ ( ውዳሴ ዘሰኑይ ገጽ 14 )

እንዲያውም ይላሉ ጸሐፊዎች ይህ ሰው « የድንግል ማርያምን ክብር ተናግሮ መፈጸም የሚቻለው አንደበት አስተውሎ የሚወስን አእምሮ የለም አንቺንም የሚመስል ማንም የለም » በማለት ሲያከብር እንደነበር ጽፈውለታል፡፡

ከእግዚአብሔር ይልቅ እነርሱ ድንግል እያሉ ለሚጠሯት ሴት ፍቅር ክብር የነበራቸው እነኝህ ሰዎች እግዚአብሔርን ማገልገል ከንቱ ነው ለእግዚአብሔርም ባርያ መሆን አይረባንም በማለት የአላማቸውን ፍጻሜ የእመቤታችን ተአምር በማለት እነሆ እስከ ዛሬ ድረስ አሜን እያሰኙ ኖረዋል፡፡

የእግዚአብሔርን የብቻው ባህርይ ሳይቀር ለእርሷ በመስጠት የሚታወቁት ጸሐፊዎች የምታደርጉትን ሁሉ በእግዚአብሔሬ ስም አድርጉት የሚለው የሐዋርያት ትምህርት ለእነርሱ የፌዝ ያህል ሆኗል፡፡ የሚገርመው በዚህ ትዕዛዘ እግዚአብሔርን የማፍረስ ትምህርታቸው ከአንባቢዎች ሆነ ከሰሚዎች ለምን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እናፈረሳለን? ለምንስ የእግዚአብሔር ባሪያ መሆን አንሻም ? በማለት የሚጠይቅ አለመነሳቱ ነው፡፡

« ሕግጋትን ልሽር አልመጣሁም የሚለውን የጌታን ቃል ተገን በማድረግ ከሕግ አንዲቱን የውጣን እንኳ አንሽራትም እያለች በምትናገረው ቤተክርስቲያናችን ያለኃፍረት 16 ቱ ትእዛዝትን ከእንግዲህ ወዲህ መጠበቅ አያስፈልገንም ብለው በቤተመቅደስ በር ላይ በድምጽ ማጉያ የሚያነቡ የሚያስነብቡ ሰዎችን ማየት በተቀደሰ ሥፍራ የጥፋት ርኩሰት ቆሞ ስታዩ አንባቢ ያስተውል የተባለው በእኛ መጀመሩ ይሆንን ? ( ማቴ 24 ÷ 15 )

ዳሩ ሕዝቡ ለረጅም ዘመን ለዚህ ዓይኑን ላፈጠጠ ጥርሱን ላገጠጠ ወንጀል በብዙ አይነት በብዙ ጉዳና ሲሰራ ስለኖረ ይቃወም ዘንድ ጥያቄ ያነሳ

ዘንድ ኃይል የለውም ::አንድም ግዝት ፈርቶ አንድም በደጋሚዎች መተት ታስሮ ::

3. <u>የማርያም ድንግልን ስም ማውሳት ብቻ ይበቃናል::</u>

ከላይ ትእዛዛቱን መጠበቅ አስፈላጊያችን አይደለም ያሉበትን ምክንያት ሲያስረዱ « የድንግል ማርያምን ስም ማውሳት ለደኅንነት በቂ ስለሆነ ነው » በማለት ያስረዳሉ:: ይህን ትምህርታቸውን የተማሩትና የቀዱት ትምህርት ቤት የት እንደሆነ መገመት ለማንም ቀላል ይመስለናል:: ጌታችን አንድ ጊዜ « እርሱ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነው » አለ ( ዮሐ 8÷44 )

ትምህርተ ሐዋርያት እንደሚያስተምረን፣መንፈስ እግዚአብሔርም እንደሚመሰክርልን፣ መጻሕፍትም ተባብረው እንደሚያስረዱት የሰዎች ድኅነት በእግዚአብሔር ምርጫ እንደተ ከናወነና ሌላም መግቢያ ቀዳዳ አለመኖሩን ሲያስረዱ « የምንድንበት ሌላ ስም የለንም » ( የሐዋ 4÷ 12 ) በእርሱ በኩል ግን የሚመጡትንም እግዚአብሔር ሊያድናቸው ወስኗል በማለት ይናገራሉ :: (ዕብ 7 ÷ 25 )

ቢጽ ሐሣውያት ግን ሰው ከኩነኔ ለመዳን ትእዛዝም መጠበቅ ሆነ የእግዚአብሔርን ሐሳብ መከተል ከንቱ እንደሆነ ይሰብኩና ከዚህ ይልቅ ዝም ብሎ የድንግል ማርያምን ስም ማውሳት ( ሳያቋርጡ መናገር ) ነው ብለውናል:: ለመሆኑ በዘመናችን በሥጋ እናቱ የሆነችው ድንግል ማርያም ብትኖርና ይህን ትምህርት ብትሰማ ምን ትል ይመስላችኋል?::

የክርስትናችንና የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከል የሆነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ ሐዋርያት አባቶቻችን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ባስተላለፉልን መልእክታቸው ለትምህርት ምሥክር ወይም ለአብነት የቅዱሳንን ስም በድክመታቸው ሆነ በብርታታቸው አንሥተው ቢጽፉም ለፈውስ ለበረከት ለጽድቅ ለቅድስና ለዘላለም ሕይወት ወ.ዘ.ተ የተጠቀሙበት ስም አንድ « ኢየሱስ ክርስቶስ » ብቻ ነበር :: የእኛዎቹ ግን « የድንግልን ስሟን ማውሳት ብቻ በቂ ነው » በማለት ይተርታሉ::

መጽሐፍ ቅዱስ ለምህረቱና ለፍቅሩ ወሰን የማይገኝለት ቸሩ አምላካችን እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ሰጠ ይላል ቅዱስ መጽሐፍ ተአምረ ማርያም

ደግሞ «እርሱ እርሷን ሰጠን» ይላል አያይዞም «የማርያም ባሪያዎች ለመሆን እንሽቀዳደም» ብሏል:: አምልኮ ባዕድን የሚያለማምደው አመንዝራው ደራሲ አብ እንኳ በማንም ላይፈርድ በረከታችንንም ሆነ ፍዳችንን ሊሰጠን የተመደበውን ጌታ ትተን ዕሩቅ ብእሲን እንድንከተል ይሰብከናል::

ሮብዓም በይሁዳ ሲነግሥ ኢዮርብዓም በ10ሩ ነገድ በእሥራኤል ላይ ነገሠ «ኢዮርብዓም በልቡ ይህ ሕዝብ መሥዋዕት ለማቅረብ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሔድ የዚህ ሕዝብ ልብ ወደጌታቸው ወደ ይሁዳ ንጉሥ ወደ ሮብዓም ይመለሳል እኔንም ይገድሉኛል አለ ንጉሡም ተማከረ ሁለትም የወርቅ ጥጆች አድርጐ እሥራኤል ሆይ ወደ ኢየሩሳሌም ትወጡ ዘንድ ይበዛባችኋል ከግብጽ ምድር ያወጡህን አማልክቶችህን እይ አላቸው::

አንዱን በቤቴል አንዱን በዳን አኖረ» /1ነገ12÷25-33/ ተብሏል ይህ ክፉ

ንጉሥ እሥራኤልን ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተጠሉ ለማድረግና የራሱን ጥቅም ለማስከበር ሲል የቃል ኪዳኑን ሕዝብ ከአምላኩ እንዳራቀውና በምትኩ የጥጃ ምሥልን እንዳቆመለት ሁሉ የእኛዎቹም ክፉዎች ከምህረቱ አዳራሽ እንድንወጣና እግዚአብሔር መድኃኒት ብሎ ያልሰጠንን እንድንቀበል ያባብሉናል

ውሉደ ዓመፃ የሆኑት እነዚሁ ደራስያን «ከልጇ ጉን በፈሰሰ ደሟ ንጹሐን ታደርገናለች» ይሉናል::

« ወስማሰ ለቅድስት ድንግል ጽሑፍ ውእቱ በቀለመወርቅ ውስተ ፍጽሞሙ ለኃጥአን ወእንዘ ይቀውም እግዚእነ ውስተ ዓውደ ፍትሕ ሶበ ይሬኢ ስማ ለድንግል ውስተ ፍጽመ ኃጥአን ይነሥት ዓውደ ወይገብእ ድኅሬሁ ምስለ መላእክቲሁ ቅዱሳን ወኵሎሙ ኃጥአን ይገብኡ ምስሌሁ ውስተ ገነተ ትፍሥሕት ዘእንበለ ሐተታ »

ትርጉም:-

« የቅድስት ድንግል ስም ግን በኃጥአን ግንባር ላይ በወርቅ ቀለም ተጽፏል ጌታችንም በፍርድ አደባባይ ሲቆም ሳለ የድንግልን ስም በኃጥአን ግንባር ላይ ተጽፎ ባየ ጊዜ ፍርዱን አፍርሶ ወደኋላ ይሸሻል ቅዱሳን መላእክቱም ከእርሱ ጋር ያለፍርድና ያለወቀሳ ደስታ ወዳለበት ገነት አብረው የገባሉ »:

4. ስሟ በኃጥአን ግንባር ላይ ይጻፋል

እግዚአብሔር የማያሻው 44 ኪርያላይሶን የሚያስፈልገው ብቻ ሳይሆን የሥጋ ዘመናችን እስኪቆረጥና ወደጌታ እስክንሰበሰብ ድረስ ዓይኖቻችን ከእንባ እንዳይቋረጡ የሚያስገድድ በቤተክርስቲያናችን ላይ የተፈጸመው ወንጀል ይህ ነው።

የጸሐፊዎች የድርሰት ዓይነት ዛሬ ምናባዊ እየተባለ በሚነገረው የሥነ ጽሑፍ ዘዴ የተከሸነ በመሆኑ ሕሊናቸውና የሚያገለግሉት የዚህ ዓለም አምላክ ያቀበላቸውን ሥዕል በብራና ላይ ሲያሰፍሩት ሃይማኖተኛ ለሆነው ሕዝባችን ለማስረዳት አይቸገሩም።

በበጎ መልኩ በቅዱሳን ግንባር ላይ ማኅተም እንዳለና እንደሚደረግ የራዕይ መጽሐፍ በምዕራፍ ሰባት ቁጥር ሦስት ላይ እንዲህ ያስረዳናል። « የሕያው አምላክ ማኅተም ያለው መልአክ ... ምድርንና አየርን ሊጎዱ ለተሰጣቸው ለአራቱ መላእክት በታላቅ ድምጽ እየጮኸ የአምላካችንን ባሪያዎች እስክናትማቸው ድረስ ምድርን ቢሆን ወይም ባሕርን ወይም ዛፎችን አትጉዱ አላቸው » ይላል።

እነዚህ በቁጥር ተለይተው ይታተሙ ዘንድ የተነገረላቸው ሰዎች ማኅተም « የሕያው አምላክ ማኅተም » በሚባል ማኅተም እንደሚታተሙ ተገልጧል።

ሌላውና መጽሐፍ ቅዱስ ሐሰተኛው ክርስቶስ እያለ የሚጠራው የእግዚአብሔር ተቃዋሚ ለሆነው ተከታዮች በግንባራቸውና በእጆቻቸው መዳፍ ላይ የሚደረገው ማኅተም ሲሆን ይህም ምልክት « የአውሬው ስም ወይም የስሙ ቁጥር ...» እንደሆነ ተገልጧል።የአውሬው ስም የተባለው በግልጥ ምን እንደሚል ባይታወቅም ይህ ስሙ በቁጥር ሲገለጥ 666 ነው ተብሏል። ( ራእ 13÷ 18 )

እንግዲህ መጽሐፍ በሕያው አምላክ ማኅተም የሚታተሙና በሐሰተኛው መሢሕ ስም ቁጥር የሚታተሙ ባሪያዎች እንዳሉ እንዲህ ተለይተው አሉ እያለ የተአምረ ማርያም ጸሐፊዎች ደግሞ ሌላ ሦስተኛ የማኅተም ስምና የሚታተሙ ሰዎችን ፈጥረው «የማርያም ስም በግንባራቸው ላይ ይጻፍባቸዋል » በማለት ጽፈዋል።

እነዚህ ሰዎች ከሁለቱ አንዱ ካልሆኑ ሌላ ሦስተኛ ማኅተምና የማኅተም ስም አለ ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ ያልገለጠ በመሆኑ ምናልባት ከሁለቱ

ባንዱ ለመደባለቅ የሚጠሩበት ኀቡዕ የብዕር ስማቸው ይሆንን

መቼም በሕያው አምላክ ማኅተም የሚታተሙት ማኅተ ማቸው የሕያው አምላክ ማኅተም ተብሎ ስለተለየና የሚያሳፍር ባለመሆኑ በኀቡዕ ስም ሆነ በብዕር ስም ለመጠራት የሚያስፈልግ ባለመሆኑ የጸሐፊዎቹ ማኅተምና የማኅተሙ ባለቤት እግዚአብሔር ወይም የእግዚአብሔር ወገኖች ሊሆኑ እንደማይችሉ ሚሊዮን ጊዜ ግልጥ ነው።

እንግዲያውስ ያልተገለጠውና ከባሕርዩውም እንደሚታየው መምሰል መለዋወጥ ልማዱ የሆነው አልያም በተቀያሪ ስም በቁጥር የተጠራው የሐሰተኛ ው ክርስቶስ ማኅተም መሆን ይኖርበታል።

ያም ሆነ ይህ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ፍጻሜ ዓለም ድረስ ያገለግል ዘንድ በተሰጠን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ « የድንግል ስሟ በቀለመ ወርቅ ሆኖ በኃጥአን ግንባር ላይ ይጻፋል» የሚል ወይም ሐዋርያት በየትኛውም የስብከትና የትምህርት ዘመናቸው ለስከንድ እንኳ ያልተናገሩት ተቀባይነትም የሌለው ወንጀል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

መቼም የፈጠራ ጽሑፍ በቤተክርስቲያናችን ተነስተው ለነበሩት መናፍቃን የማይነጥፍ ችሎታና ጸጋቸው ( ከአጋንንት) ሆኖ ዓለም ቢያደንቅላቸውም ለልብ ወለድ ጽሑፍ በታሪክ ለሀገሪቱ አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ቢደነቁም መንፈሳዊ ሽፋን እየቀቡ ወደ ቤተ መቅደስ ማስገባታቸውን ግን ያለርኅራኄ የምንቃወመው ነው፡

## 5. ኢየሱስ በኃጥአን ግንባር ላይ ያለውን የድንግልን ስም ይፈራዋል

እንደደራስያኑ ሐሳብ ይህችው እነርሱ ማርያም የሚሏትን ሴት ስም በግንባራቸው ላይ የያዙ ኃጥአን ለፍርድ እንዲቀርቡ ሲደረግ ፈራጁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፍርድ ወንበር ሲቀመጥ ታትሟል የተባለውን ስም ሲመለከት ደንግጦ ሊፈርድ የመጣበትን ጉዳይ ሁሉ ትቶ በአንድ ሰው ላይ እንኳ ሳይፈርድ ወደ መጣበት ይመለሳል ይሉናል።

እንዴት የትምህርት መፋለስን ወደ ቤተክርስቲያኒቱ እንዳስገቡ ያለከልካይም ያሻቸውን ማለት እንደቻሉ ተጨማሪ መረጃ ነው።

<u>*ጌታችን ኢየሱስ ለምን ፈራ ?*</u>

ደራስያኑ እንዳስቀመጡት በኃጥአን ግንባር ላይ የተጻፈውን ስም ሲያየው ለመቀመጥ እስኪያቅተው ድረስ ኃይል በግባንራቸው ላይ እንዳየ አሳይተውናል።

ይሁን እንበልና ተረቱ በሥጋ የወለደችው በቤቷ ያሳደገችው በመስቀሉ በስደቱ አብረው የነበረችው የእናቱን ስም ከሆነ ምን አስደነገጠው? እንደገናም የጌታችን ባሕርይ የሚጠላውና የሚያስቆጣው የሰይጣን ግብር ብቻ እንጂ የማርያም የእናቱ /በሥጋ/ ስም ነው አንልም::

ሌላው እናቱ ማርያም እንኳ ይህን አድርጋ ተገኝታ ቢሆን ጴጥሮስ እንቅፋት ሲሆነው (ማቴ16 : 23 )በግብዝው ቤት ተጠርቶ ግብዝነታቸውን አይቶ ( ሉቃ 7 ÷ 36 - 50 ያዕ 2÷ 1- 7 ) ያለ ሐፍረት ያለ ይሉኝታ ሳይሳቀቅ እንደገሰፃቸው በገሰፃት ነበር እንጂ ይህን የሚያህል ወንጀል ሠርታ ይልኙታ ይዞት ፈርቶ ይሄዳል ማለት ባሕርዩን መንቀፍ ይሆናል::

የሚገርመው በዚህ በኃጢያተኞች ላይ ተጻፈ በተባለው ስም ምክንያት አብ በመጨረሻው ዘመን በሙታንና በሕያዋያን ላይ ይፈርድ ዘንድ ፍርድን ሁሉ የሰጠውን ወልድን ይህ የማርያም ስም እንዳይፈርድ የሚያደርግ ጉልበት አለው ማለታቸው ነው :: በጸሐፊዎቹ ሐሳብ ማንም ኃጢአተኛ የማርያምን ስም በግንባሩ ላይ ከጻፈ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ በኃጢአታቸው ምክንያት መፍረድ ስለማይችል በደሉ ሳይታሰብበት ስተት ብሎ መንግሥተ ሰማያት ይገባል ማለታቸው ነው::

ለመሆኑ ጸሐፊዎቹ ማርያም እያሉ የሚጠሯት በእርግጥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ናትን ?

ይህን ለማለት ያነሳሳን ለቅዱሳን የማይገባውን ነውር ቅዱሳን ተናግረውታል እየተባለ በመናፍቃኑ በመጻፉ ነው:: ለምሳሌ በውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ላይ ውዳሴዋን ጻፈው የሚባለው ሰው ለመጸፍ ከመነሳቱ በፊት ጸሐፊዎቹ እንዳሉት « ሰውየው ( የማርያም ውዳሴ ነው የተባለውን መጽሐፍ ጻፈ ያሉት ) እልፍ ከአራት ሽህ ድርሰት ጽፎላታል » ይላሉ:: እንደገናም በቀን ስልሣ አራት ስልሣ አራት ጊዜ ይደግመው እንደነበር ጽፈውለታል :: ይህን ሲያደርግ ይላሉ የድርሳኑ አራጋቢዎች « እመቤታችን ትመጣለች ( ከየት ? ) ያንጊዜም የብርሃን ምንጣፍ ይነጠፋል የብርሃን ድባብ ( እንደ ድንኳን ያለ ) ይዘረጋል : ከዚያ ላይ ሆና ( ተቀምጣ ) « ሰላም ለከ አ ፍቁርየ ኤፍሬም » ትርጉም « የምወድህ ኤፍሬም ሆይ ሰላም ላንተ ይሁን » ትለዋለች:: እርሱም ታጥቆ እጅ ነስቶ ይቆማል:: እርሷም « ወድስኒ » ( አመስግነኝ ማለት ነው ) ትለዋለች:: እርሱም « እፎ እክል ወድሶተኪ ዘኢይክሉ ሰማያውያን

ወምድራውያን » ይላታል ( ምድራውያን ጻድቃን ሰማዕታት ሰማያውያን መላእክት አንቺን ማመስገን የማይቻላቸውን እኔ እንደምን ይቻለኛል ማለቱ ነው ። ከዚያ በኋላ ተባርኮ ውዳሴዋን ይጀምራል ይላል፡፡

በዚህ ጽሑፍ ጸሐፊዎቹ የገለጧት ሴት በእርግጥ የጌታችን እናት እንዳይደለች ቁልጭ አድርገው አሳይተውናል፡

1ኛ. በነቢዩ በኢሳይያስ ትንቢት ምዕራፍ 42 ፥8 -9 ላይ « እኔ እግዚአብሔር ነኝ ስሜ ይህ ነው ክብሬን ለሌላ ምሥጋናዬንም ለተቀረጹ ምሥሎች አልሰጥም » የሚለውን ሕግ በመጣስ በድንግል ማርያም ስም እልፍ ከአራት ሺህ የሚሆን ምሥጋናን ደርሶ ያመሰግናት ያስመሰግናት ነበር ማለታቸው ።

2ኛ. እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት ዕለት ዕለት እግዚአብሔርን ማመስገን ለእግዚአብሔርም ዝማሬን ማቅረብ መልካም ነው ፡ ( መዝ 97 ፥ 1-2 ) እንዲያውም በመዝ 102 ፥ 1 - 6 ላይ ዳዊት ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ ይልና አጥንቶቼም ሁሉ በማለት በሁለንተናው ለእግዚአብሔር ምሥጋናን ለማቅረብ ይመኝ ያደርገውም እንደነበር ገልጦ ተናግሯል፡፡ ምድር ሁሉ ለእግዚአብሔር እልል በሉ ተብሎ ( መዝ 99 ፥ 1 ) እያለ ኤፍሬም የተባለው ሰው ግን ፋታ ሳይሰጥ በየቀኑ ስልሣ አራት ስልሣ አራት ጊዜ የደረሰውን ድርሰት እየደገመ ሲያመሰግናት መታየቱ

3ኛ. ይህን ምሥጋና ለመቀበል ትመጣለች የተባለችው የሚደረግላት ሥርዓት ነው ይኸውም የብርሃን ምንጣፍ ተነጥፎ የብርሃን ድንኳን ተደኩኖ በዚያ ላይ ሆና እየሰገደ የሚያቀርብላትን ምሥጋና መቀበሏ፡ በግልጥም ያለፍርሃት « ወድሰኒ » አመስግነኝ አለችው የሚለውን ቃል ስናይ እንደፈጣሪ ምሥጋናናን ለመቀበል የፈለገች ሴት አድርገው በማቅረባቸው የጌታችን እናት አይደለችም ብለን አፋችንን ሞልተን እንድንናገር ያበቃናል፡፡

በሩቅ ምሥራቅ ሰዎች ዘንድ የምትታወቅና በእኛ ጸሐፊዎች የተሰጣትን ገፀ ባሕርይ የተላበሰች እነርሱ «የሰማይ ንግሥት» የሚሏት ጣዖት አለች:: ምናልባትም ጸሐፊዎቻችን ከዚያ ቀድተው ይሆን::?

በተክለ ጻድቅ መኩሪያ መጽሐፍ ላይ ዘርዓያዕቆብ የተባለው የድርሳንና የገድል አፍቃሪ ጸሐፊና አጻፊ ንጉሥ ሩቅ ምሥራቅ ሄዶ እንደነበር ከዚያም መጻሕፍትና ባህል ሥርዓት ይዞ ሳይመጣ እንዳልቀረ ጽፈዋል:: ( ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ዐጼ ዮሐንስ እና የኢትዮጵያ አንድነት )

ይህ ከሆነ ደግሞ የመጻሕፍቶቻችን የትምህርቶቻችንና የሥርዓቶቻችን መበከል ምክንያቱ አንዱ ይኸው ሊሆን እንደሚችል መገመቱ አያዳግትም::

## ሐዋርያው ጳውሎስን በደማስቆ መንገድ ላይ በታላቅ ብርሃን ተገልጣ ወደ ጽድቅ የመራችው ድንግል ማርያም ናት

ተአምረ ማርያም

*« በእንተ ጳውሎስ ሐዋርያ*
*ስለ ሐዋርያው ጳውሎስ»*

ልመናዋ ክብሯም በኛ ለዘላለም በእውነት ይደርብንና አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች ክብርት እመቤታችን ያደረገችው ተአምር ይህ ነው::

ቅዱስ ጳውሎስ በሁለተኛ የቆሮንቶስ መልእክቱ እንደተናገረው መላእክት እስከ ሦስተኛ ሰማይ አሳርገውት ሳለ አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ስለ ጸናች ስለ ክብርት እመቤታችን ክብር ሲናገር እንዲህ አለ::

እኔ ጳውሎስ ገና አብያተ ክርስቲያናትን በማፈራርስበትና የጌታን ደቀ መዛሙርት ለመግደል በማሳድድበት ጊዜ ይልቁንም በየመንደሩ እየገባሁ ወንዶችንም ሴቶችንም እየጐተትኩ ወደ እስር ቤት በምጨምርበት ወቅት እነሆ ከዚያ ምእመናንን እያደንኩ የምይዝበት የሥልጣን ደብዳቤ ይዤ ወደ ደማስቆ ስጓዝ ድንገት ከሰማይ ጸዳል አንጸባረቀብኝ::

በዚህም ጊዜ በምድር ላይ ወደቅሁና እነሆ በሰው ልጅ አንደበት ሊነገር ወይም ሊተረጐም የማይችል ቃል ሰማሁ:: ከእኔም ጋር ቆመው የነበሩ ሰዎች ድምፁን ከመስማት በቀር ማንንም አላዩም:: በመሬትም ላይ ወድቄ እየተፍገመገምኩ ሳለሁ እኔን ጭንጋፍ የሆንኩ ሰው መላእክት መጥተው አጽናኑኝ አንሥተውም እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ አሳረጉኝ::

በዚያም ጊዜ የደም ግባቷ ጸዳል እንደፀሐይ የሚያበራ ድንግል ከሩቅ ስትመጣ ተመለከትኩ:: ከእሷም ጋር ሁለት መቶ መላእክት በፊትና በኋላዋ ሆነው እየዘመሩ መጡ:: ከእኔም ጋር ያለውን መልአክ ይህች ማናት? በዚህን ያህል ክብር ክብራ የምትመጣ አልሁት:: መልአኩም ይህች አንተ የምታሳድደው የናዝሬቱ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ናት አለኝ:: በዚያም ጊዜ ወደ እኔ መጣችና ሰላም ካለችኝ በኋላ ሳውል ሳውል ልጄን የናዝሬቱ ኢየሱስን ለምን ታሳድደዋለህ? የሾለውን ብረት ብትረግጥ ለአንተ ይብስብሃል::

እኔም እየፈራሁና እየተቀጠቀጥሁ እመቤቴ ሆይ ስለ ኃጢአቴ ምን አደርግ ዘንድ ይገባኛል የሰው ደም እያፈሰስኩ ወንጀለኛ ሆኛለሁና አሁንም እመቤቴ ሆይ ኃጢአቴን ይቅር በይልኝ እነሆ አንቺ እናቱ እንደሆንሽ ተገልጾልኛ ልና አልኩ፡እሷም እነሆ ኃጢአትህ ይሰረይልህ ዘንድ ስለ ለመንኩልህ እነሆ ኃጢአትህን ይቅር ብሎሃል አሁንም በሕይወተ ሥጋ ሳለህ ወደዚህ ትመጣ ዘንድ ልጄን ኢየሱስ ክርስቶስ ማለድኩት እሱም እሺ ጥቂት ታገሺ አመጣዋለሁ አለኝ::

ይልቁንም አቤቱ ልጄ ወዳጄ አታዘግይብኝ ፈጥኖ ልታመጣው እወዳለሁ በእሱ የትምህርት ዘመን ስምህ እጅግ እንዲመሰገን ታውቃለህና አልኩት:: ልጄ ወዳጄም አዎን እናቴ ሆይ በአሕዛብና በነገሥታት በእስራኤልም መካከል የሞቴን መስቀል ተሸክሞ በጣፈጠ አንደበቱ በቀለጠፈ አነጋገሩ በታማኝነቱ የወንጌል መንግሥት ያስተምር ዘንድ የተመረጠ ዓርበኛ አድርጌ እልክዋለሁ አለኝ:: በስሜ ብዙ መከራ ይቀበል ዘንድ አለው ብሎሃልና ስለዚህ በሥላሴ ስም ተጠመቅ:: እነሆ አሁንም ቅዱሳኖች ሁሉ ታላቅ አቀባበል ያደርጉልሃል አለችኝ::

ይህች ድንግል እንዲህ እያለች በምትነግረኝ ጊዜ እነሆ ፊታቸው ብሩህ የሆነ ሦስት ሰዎች መጡ:: ከእኔ ጋር የነበረውን መልአክ እሊህ እነማን ናቸው? ብዬ ጠየቅሁት:: እሱም እሊህ አባቶች አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብ ይባላሉ አለኝ::

እነሱም መጥተው ለእመቤታችን ሰገዱ እኔንም ሰላም አሉኝ እኔም እጅ ነሣኋቸው።

ከዚህም በኋላ እመቤታችን ከሷ ጋር ከነበሩ መላእክት መካከል ሦስቱን በዮርዳኖስ ውሃ ያጠምቁኝ ዘንድ ነገረቻቸው። እኔም ተጠመቅሁ የመንፈስ ቅዱስም ኃይል መላብኝ አደረብኝ። በዚያም ጊዜ በደሌ ሁሉ ከዓይኖቼ እንደ ቅርፊት እየተቀረፈ ወደቀ። ብርሃንም መላብኝ ዓይኖቼም ተከፈቱ ያንጊዜውንም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ለማስተማር አፋጠን ጀመር።

ይህንንም ያዩ ሁሉ አደነቁ እንደዚሁም በይሁዳና በገሊላ በሰማርያም የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ዕረፍት አገኙ በእግዚአብሔር ቸርነት በመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት እየተስፋፉና እየጸኑ ሄዱ ቅዱስ ጳውሎስ ለዚህ ክብር በተጠራ ጊዜ። እናንተ የእግዚአብሔር የወንጌሉና የሰላም ልጆች አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች የክብርት እመቤታችንን ጳውሎስ ያየውን ክብርና መላእክት በፊት በኋላዋ ሆነው እየዘመሩ ሲያከብሯት ተመልከቱ። እነሆ አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች የክብርት እመቤታችን ምስጋና በምድር ብቻ ሳይሆን በሰማይም በመላእክት አንደበት ይነገራልና። እንግዲህ ጳውሎስን መላእክት እንዳከበሩት እኛንም ያከብሩን ዘንድ ባለን ኃይል ሁሉ እመቤታችንን ማመስገን ይገባናል። ይልቁንም ጳውሎስን ከፈጣሪዋ አማልዳ ለጌታው የተመረጠና የታመነ አገልጋይ እንዳደረገችውና ከሐዋርያት ማዕረግ እንደ አደረሰችው የቸርነቷን ብዛት እናስተውል። የእኛንም ጸሎታችንንና ልመናችንን ለዘለዓለሙ ክብር የተገባው ወደ ልጅዋ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ታሳርግልን ከወዳጆቹ ከቅዱሳን ጋር አንድ ያደርገን ዘንድ ለዘለዓለሙ። ልመናዋ ክብሯ በእውነት ለዘለዓለሙ በኛ ይደርብን።

/ተስፋ ማተሚያ ቤት በ1983 የታተመ 97ኛ ተአምር/

# መጽሐፍ ቅዱስ

*ስለ ሐዋርያው ጳውሎስ*

ሲሄድም ወደ ደማስቆ በቀረበ ጊዜ ድንገት በእርሱ ዙሪያ ከሰማይ ብርሃን አንጸባረቀ በምድርም ላይ ወድቆ ሳለ:- <u>ሳውል ሳውል ስለ ምን ታሳድደኛለህ? የሚለውን ድምፅ ሰማ። ጌታ ሆይ ማን ነህ ? አለው። እርሱም:- አንተ</u>

የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስብሃል አለው፡፡ ሐዋ.ሥራ 9:3 - 6 /የሉቃስ ምስክርነት/

ስሄድም ወደ ደማስቆ በቀረብሁ ጊዜ ቀትር ሲሆን ድንገት ከሰማይ ታላቅ ብርሃን በዙሪያዬ አንጸባረቀ በምድርም ላይ ወድቄ፡- ሳውል ሳውል ስለ ምን ታሳድደኛለህ? የሚለኝን ድምፅ ሰማሁ፡፡ እኔም መልሼ፡- ጌታ ሆይ አንተ ማን ነህ ? አልሁ፡፡ እርሱም፡- አንተ የምታሳድደኝ የናዝሬቱ ኢየሱስ እኔ ነኝ አለኝ፡፡ ሐዋ.ሥራ 22:6 - 9 /የጳውሎስ ምስክርነት/

# ምዕራፍ አምስት

# ሌሎች መጻሕፍት

## አብ በከንቱ ደከመ

በማትመረመር ሐሳቡ ማንም ሊደርስበት በማይችል ፈቃዱ የሁላችን ኃጢአት መወገጃው በእርሱ እውቀት «የኢየሱስ ሞት» እንደሆነ በመፍቀዱ ኢየሱስ በሥጋ ተገለጠ።

መላእክት « እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና » ( ማቴ 1፥21) እንዲሁም እርሱ ክርስቶስ መድኃኒት ተወልዶላችኋል አሉ (ሉቃ 2፥11) በዚህ ላይ አስተያየት ጥቆማ ጥያቄ በቅርብ ወይም በድምጽ ብልጫ ለመወሰን የምንችለው ጉዳይ ሳይሆን «አሜን» የምንለው /እርሱም እግዚአብሔር ሲረዳ ነው/ የማይቀለበስ የልዑል ውሳኔ ነው። ስለሆነም ከእኛ የሆነ ምንም ሳንጨምርበት በእርሱ ሥራ የተፈጸመውን የእግዚአብሔር ፈቃድ በመቀበል ስንገኝ አሁንም በእርሱ ውሳኔ መሠረት «ጻድቃን ቅዱሳን» ተብለን እንድንጠራ ወዷል። ይህ የእግዚአብሔር የራሱ ፈቃድ ስለሆነ አሜን አልን እንጂ እኛ በግብር ጻድቀን ቅዱሳን ሆነን ተገኝተን አይደለም። እርሱ ግን ይሁን ካለ መጽሐፍ እንዳለ «ሆነ» እንላለን ። ይህን የእግዚአብሔር ሐሳብ በማወቅና በማመን ለተቀበሉ ሁሉ ( ገና ያልተረዳነውና ያልተገለጠው) ግን እግዚአብሔር ለሚወዳቸው ያዘጋጀው ሁሉ ለእነርሱ ተመድቦላቸዋል። 1ኛ ቆሮ 2፥ 9 - 10 / የክርስትና እውነት ይህ ሆኖ ሳለ ይህንንም መመስከር ማስተማር ግብራችን ሆኖ እያለ በኋላ የበቀሉ ከዓሣ ጋር የተደባለቁ ጊንጦች ይህን የእግዚአብሔር ሐሳብ ወደ ጐን በመተው እንዲህ ይላሉ።

ማንም ስሙንና የልጁን ስም ወለተ ሚካኤል ገብረ ሚካኤል /ወለተ/ ገብረ ማርያም ብሎ የሰየመ ሁሉ በዚህ ስም ምክንያት መንግሥተ ሰማያት ስተት ብሎ ይገባል በማለት ይናገራሉ።

( ድርሳነ ሚካኤል ተአምረ ማርያም )

ጽድቅ ቅድስና ጥበብና ቤዛነት «በክርስቶስ» /ሆነ ተብሎ (1ኛ ቆሮ 1፡ 31) እያለ በሚካኤልና በማርያም ስም ስሙን የጠራ ይጸድቃል የሚለው ክህደት መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ እንዳሉ ሰይጣንን አንተ ቅዱስ ብንለው ከቶ

ከባሕርዩ ፈቀቅ እንደማይል ሁሉ እንዲሁ መሆናቸው ነው። እንኪያስ በስመ ሚካኤልና ማርያም ቀርቶ /ወለተ/ ገብረ ኢየሱስ ወለተ ገብረ አብ /ወለተ/ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ብለን ብንሰይም ማንም አይጸድቅም በብሉይ ኪዳን እንደነበረው ስም ግብርን ይገልጣል የሚባለው ዛሬ የሚሠራ አይደለም። አይሆንምም። ገብረ ኢየሱስ ሆኖ በአማናዊ ግብሩ ገብረ ዲያብሎስ ሞልተውናልና።

ስለሆነም በዚህ ትምህርት ተጠምደው ያሉ ቤተሰቦቻችን ስምን በሚወዱት ጻድቅና ቅዱስ መልአክና በእግዚአብሔር እየለጠፉ ቢያወጡት በኢየሱስ ብቻ አምኖ ካልኖሩ ጽድቅ እንደሌለ ያውቁ ዘንድ ይህን መጽሐፍ ለሚያነቡ ሁሉ ኃላፊነታቸው ነው እንላለን።

# ሚስቱ መበለት ትሁን ልጆቹም ይበተኑ

በዚህ ርዕስ ደስ ብሎት አሜን ይሁን ይደረግ ለማለት ከዚህ በፊት አልያም በኋላ ያለውን ሙሉውን ሐሳብ ካልተረዱ አሜንታዊ አደጋ ሊኖረው ይችል ይሆናል።

ምክንያቱም መጽሐፍ እንደሚለው ሰው የሚባለውን ሰምቶና ለይቶ ሲገባው የሚጠቅመው ከሆነ «አሜን» ይላል እንጂ ካልሆነ አለመተባበር እንደሚገባ ያስረዳሉ ። ሆኖም ብዙው የቤተክርስቲያናችን ምዕመን አገልጋዩቹን በእግዚአብሔር ፈንታ ስለተቀበላቸው ብቻ የአገልጋዮች ከንፈር ይንቀሳቀስ እንጂ ፈጥኖ እልል አሜን ማለት ፍጥነቱን መላእክት እንኳ አይቀድሙትም።

አንድ ጊዜ በአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ሰባኪው አዳም አትብላ ተብሎ የታዘዘውን በመጣሱ እግዚአብሔር እርቃኑን አስቀረው ወደ ምድረ ፋይድ ሰደደው የታአባቱ —ብለው ሞቅ ሲያደርጉት በሐሳብም በመንፈስም በእግዚአብሔር ፊት የሌለው ሕዝብ በአካል « እልልል —— » በሚል ድምፅ ጉባኤውን አቀለጠው።

በተገኝበት ቁጥር ቤተክርስቲያን ሆኖ ከሐሳቡ ስመመን አለሁ ለማለት ያህል እልል.. ይበል እንጂ ምን እንደተባለ እንኳ አያውቅም

አንድ ሰው ከዓውደ ምህረቱ ራቅ ብሎ በቆመበት ሥፍራ ጓደኛው ዘግይቶ ሲደርስ ድንገት ቅልጥ ያለ ሳቅ ዓውደ ምህረቱን ሞላው ያ ዘግይቶ የመጣ ሰውም «ለመሆኑ ምንድን ብሏቸው ነው ሰባኪው ሲናገር ሕዝቡ የሳቀው

አለው:: እኔ እንጃ አለ ታዲያ አንተ ለምን ሳቅህ ሲለው እንዲያው በጸጋው ነው» አለው::

ይህ እንዲያው በጸጋው ነው በሚል ሽፋንና ከቤተመቅደስ መቼም ክፉ ነገር አይገኝም በሚለው የዋህነት አሜን ማለትና አብሮ መደለቁ ብዙዎችን ያለ ክርስቶስ እንዳስቀረ ምሥክር እንጠቅሳለን::

ያለ አስተርጓሚ በሚነበነበው ቋንቋ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ በሚነገሩ ማደናገሪያዎች አልያም ከአማርኛ ጋር ቅርበት ያላቸው ቃላትን በመደባለቅ ተፈላጊውን ድጋፍ ለመቀበል በማድረግ ጥበብ ሕዝባችን ተታሎ ይኸው ያለ ክርስቶስ አለ::

ያላነበበውንና ትርጉሙን ያልተረዳውን መጽሐፍ እየተሳለመ ሰውነቱን እያሻሸ የሚሄደው ሕዝባችን መተኪያ የሌላትን ነፍሱን ለአገልጋዮቹ አደራ ሰጥቶ የሚኖር ነው::

ከዚህ የተነሣ እርሱ ያለ ክርስቶስ የሆነውን የመጽደቅ ሙከራ ማለትም በምግባር በትሩፋት ሊጸድቅ የሚደክምበትን ኃሳብ አልሳካ ሲለው በቅዱሳኑና በመላእክት በዓላት ዝክር ማድረግን ጨምሮ ዕረፍት ባለማግኘት በመጨረሻም ነፍሱ ከሥጋው ስትለያይ እንኳ ወዴት እንደሚሄድ ባለማወቁ ሲኦል እንዳይገባ በቀሪ ዘመዶቹ ላይ ተበድረው የማይጨርሱትን ዕዳ /ከ7ቀን - 7 ዓመት/ ጥሎላቸው ያልፋል::

ያሳደጉት አገልጋዩቹ ደግሞ የደነገጉትን ሥርዓተ ፍትሐት ቤተሰቦች ካሟሉ እንደ ቢሮ ሥራ የቆጠሩትን የፍትሐት ሥርዓት ለማድረግ ቃል ይገቡለታል::

ይህ የሙታን ፍትሐት ሥርዓት በሕዝባችን ዘንድ የተወደደ የተለመደና በሰባኪዎችም አስፈላጊነቱ ስለሚገለጥ ፍትሐት ከሚያጣ ራሱን ክርስቶስን ቢያጣው እንኳ የሚመርጠው ባህሉ ሆኗል::

<u>ፍትሐት ምንድን ነው?</u>

በሠራተኞቹ አገላለጥ ፍትሐት አገልጋዮች /የመቅደሱ/ ሟቹ ያልተናዘዘበት ኃጢአት ቢኖርበትና በዚህም ምክንያት ወደ ሲኦል ቢጣል በሚደረገው ጸሎትና ምልጃ ወደ ገነት ይዛወር ዘንድ እግዚአብሔርን የመለመን የመጠየቅ ሥርዓት ነው:: ይህም እናንተ ያሠራችሁት የታሠረ ይሆናል፣ የፈታችሁት የተፈታ ይሆናል ተብሏልና ይላሉ::

ሆኖም ፍትሐት የሚለውን ሐሳብ የቀደሙትና ደጋግ የተባሉት ክርስቲያን አባቶች ይጠቀሙበት የነበረው ክርስቶስን በማመን ደህንነትን የተቀበለ አንድ ሰው ይህን ኀብረቱን በጥምቀቱ በአደባባይ በመመሥከር የቤተክርስቲያን /ከቅዱሳን ጋር/ አባልነቱን ሲገልጥ ቤተክርስቲያን ለጌታ ሥራ እንደተቀበለችው እንዲሁ በምድር አገልግሎቱን ፈጽሞ ወደ ጌታ ሲሰበሰብ ቤተክርስቲያን ወደ እረፍት የሄደውን ሰው አስክሬን በክብር አምላካቸውን እያመሰገኑ እስከ ጊዜ ትንሣኤ ይቆይ ዘንድ ወደ ተዘጋጀለት ምድር ለመሸኘት የሚደረግ ሥርዓት እንጂ የጐደለ ጽድቅ ለመሙላት ያልታረመ ኃጢአት ለማረም አልነበረም:: /ይደረግ ቢባል እንኳ የሚደረግ አይደለም

ይህን አባባል የሚደግፍልን ከጸሐፊዎቹ ዓይን ተጋርዶ ግን በፍትሐት የሚቹን ኃጢአት እናስተሰርያለን በሚሉት ተጽፎ ያለፈ ጽሑፍ እንዲህ በማለት ያፈርስባቸዋል « እምድኅረ ሞቱ ለሰብእ አልቦቱ ንስሐ » (መጽሐፈ ግንዘት) ይህ አንቀጽ በአንዳንድ የግንዘት መጻሕፍት ፍቀው በማውጣት እንዳይታይ አድርገዋል ሆኖም በዚያው በያዙት መጽሐፍ ላይ የዚህ ተመሳሳይ እንዳለ ማሳየት እንወዳለን::

« እስመ አኮ በውስተ ገሃነም ዘቦ ንሥሐ ወአኮ እምድኅረ ሞት ዜና ዕረፍት » ትርጉም « በገሃነም ንሥሐ የለም ከሞት በኋላ እረፍት የለም » *መጽሐፈ ግንዘት ገጽ 196 እንዲሁም በትዕዛዙ ገጽ 7 ላይ ( በዚሁ መጽሐፍ )* እምድኅረ ሞቱ ለሰብእ አልቦቱ ምሕረት »

ያሠራችሁት የታሠረ የፈታችሁት የተፈታ ይሆናል የሚለውን ቃል እውነተኛ የቤተክርስቲያን መምህራን ሲተረጉሙት ሰውየው በሕይወቱ እያለ ቃለ ወንጌልን ሰምቶ ተረድቶ ወደ ክርስትና ቢቀላቀል ይህ ሰው በትምህርተ ወንጌል ከነበረበት የኃጢአት እስር ተፈትቶ መጥቷልና ጌታችን ፈታችሁት አላቸው :: ይህ ሰው የእናንተን ምስክርነት የሰማ እኔን ሰምቷል እንዳለ ጌታ በሰማይም የተፈታ ነው አላቸው እንዲሁም የወንጌልን ቃል ሰምቶ ግን አቃሎ በክርስቶስ ማመንን አሻፈረኝ ቢል በቤተክርስቲያን የተነቀፈ በእግዚአብሔርም ጽድቅ ያልታሰበ ሆኗልና ከቤተክርስቲያን ተለይቷል /በዚህ ዓለም ኃጢአትና አገዛዝ ተይዟል/ ማለት ነው እናንተ ያልተቀበላችሁት /ወንጌልን ባለመቀበሉ/ በሰማይም እንዲሁ ነው ሲል ያሠራችሁት አለ ይላሉ::

የእኛዎች ግን የሚካኤል ዕለት አርሠሃል እንጨት ሰብረሃል የገብርኤል ዕለት ሥራ ሠርተሃል ወ .ዘ .ተ እያሉ ገዝቼሃለሁ /አስሬሃለሁ/ በማለት ማሰርና

መፍታትን የሥልጣን ባሕርይና የግል ሹመታቸው አድርገው ተጠቅመውበታል።

የቤተክርስቲያናችን ሕዝብ ግን ይህን ሳይረዳ የካህናት ጸሎት ሳይደርስለት እንዳይቀበር በማለት አስከሬን በመያዝ ቤተክርስቲያን ይመጣል። በመጣው አስክሬን ላይ ምን እንደተባለ ሳያውቁ እንበል አቡነ ዘበሰማያት ሲባል ብቻ አሜን ይላል።

የመጽሐፈ ግንዘት አፈጣጠር

አንድ ክፉና ጨካኝ እግዚአብሔርንም የማይፈራ ዘመኑን ሁሉ በዝሙትና በርኩሰት እያሳለፈ የነበረ ሰው ነበር ። ይህ ሰው በሞተ ጊዜ በጊዜው ኤጲስ ቆጶስ የሆነ ልጅ ነበረው ይላል የፈጣሪዎቹ ትረካ። ልጁም ( ኤጲስ ቆጶሱ ) ለሞተው አባቱ ለ6 ቀናት ያህል አለቀሰለት በዚህ ጊዜ ነፍሱ በሲኦል እንዳለች አወቀ።

በመጨረሻም መልአኩን በጠየቀው ጊዜ ክፉዎች ንሥሐ ያልገቡ እዚህ ገሃነም እንደሚገቡ ሲነግረው ለ40 ቀናት ያህል ቁርባን እያስወጣ አስቀደሰለት አስጸለየለት ወይም አስቆረበለት። ( የሚበላ ድግስ እያስደገደሰ ማለት ነው። )

በዚህ ሥርዓት መሠረት በሲኦል ነበረ የተባለ አባቱ ከሲኦል ውስጥ ከአንገት በላይ ብቻ ብቅ ብሉ ታየው በዚህ የተነሳ እስከ 7 ዓመት እየጸመ ሲያስቆርብለት ነፍሱ ከገሃነም ሙሉ በሙሉ ወጥታ ገነት መንግሥተ ሰማያት ገባች ይላል ተረቱ።

ስለዚህ ይህ የግንዘት መጽሐፍ አገልግሎቱ ለሕዝቡ ደርሰ ዘንድ ይህን እንደጻፉ ጸሐፊዎቹ ሳያፍሩ ጽፈውታል። ( ግንዘት ገጽ 215 )

ጦር ሜዳ ፣አውሬ በልቶት ፣ውኃ ወስዶት፣አስክሬኑ የጠፋ ሰው ካልሆነ በስተቀር ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ደርሶ ጸሎተ ፍትሐት ሳይደረግለት የተቀበረ ሰው በቤተክርስቲያን አለ ብንል ምናልባትም በዘመነ ሶሻሊዝም ብቻ ነበር ያም ቢሆን አስከሬኑ ቅጥረ ቤተክርስቲያን ባይገባም ጠበል ጣዲቁ ተዘጋጅቶ በየስማቸው ፍትሐት ሳይደረግላቸው አይቀሩም።

በፍትሐት ሕግ መሠረት ታንቆ የሞተ ገደል ገብቶ የሞተ ዛፍ ሲቆርጥ ወድቆ የሞተ ውኃ የወሰደው ሰው ፈጽሞ ፍትሐት የማይደ ረግለት እንደሆነ የታወቀ ነው። የፍትሐቱ ዓላማና ፋይዳ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ የሌለው ከመሆኑም ባሻገር እውነተኛውን የእግዚአብሔር ቃል የሚቃረን መሆኑ ነው።

የፍትሐት ሥርዓት ባለሙያዎች እንደ ሚሉት የሟቹን ኃጢአት ለማስተስረይ ካህናት በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት ማስፋት ስለሚችሉ የእነርሱ ፍትሐትና የሟቹ ቤተሰብ ከገቀን-ገዓመት ድረስ ያለው ድግስ ተደምሮ እንኳን ተረስታ ያልተናዘዟትን ትንሽዋን ኃጢአት ይቅርና ሲኦል እንኳ ገብቶ ቢሆን ወደ ገነት እንዲገባ ሊያደርጉ እንደሚችሉ ይናገራሉ::

ፍትሐቱን ፈላጊዎችና የሟቹ ቤተሰቦች ይህን ስብከት ተቀብለው ሰው ደካማ ነውና በካህናቱ ጸሎት ኃጢያቱ ተሰርዮለት ገነት መንግሥተ ሰማያት ይገባል በማለት የደንቡን ፈጽመው ያስፈታሉ::

በእርግጥ ካህናቱ ፍትሐቱ ምንም ፋይዳ እንደሌለው ቢያውቁም ሥርአተ ፍትሐቱ «ደጀ ሰላሙ እንዳይዘጋ» የሚያደርግ በመሆኑ ከመተዳደሪያም አቅም ማነስ አኳያ የዕለት ጉርስ ማግኛ ዘዴ በመሆኑ ቢሰለቹም ሥር አቱን ማከናወን አይተውም ::

ወንጌላችን:- «በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስለማያምኑ አሁን ተፈርዶባቸዋል ይላል »ዮሐ 3-19 የመቅደሱ ሰዎች ይህ ሰው ቢሞት እንኳ በፍትሐቱና በድግሱ ጥምረት እንደሚያድኑት ያሳስባሉ « ዘይገብር ተዝካረክ ኩሉ ሰብእ እምድኅረ ሞቱ አቡሁ ወእሙ ወወረዱ ውስተ ሲኦል አወጽኦሙ እም ውስተ እሳት »ትርጉም « መታሰቢያህን የሚያደርገውን ሁሉ እናትና አባቱ ቢሞቱ ወደ ሲኦልም ቢወርዱ ለእሳት አወጣቸዋለሁ » ብሏል በማለት ይቀልዳሉ / ገ.መ.ቅ. 27-9/

ስለፍትሐትና ድግሱ ብዙ ማለት ብንችልም ለዛሬው ግን ለሟቹ የሚደረገው የፍታት ጸሎት ምንነት በማሳየት ምን ያህል ሕዝባችን/ምዕምናን/ በማያውቁት ከንቱ ነገር ሲረገሙና ሲያስረግሙ እንደኖሩ እናያለን :: በቤተክርስቲያናችን የመቅደስ ሠራተኞች ሕግ መሠረት የሟቹን ኃጠአት ለማስተስረይ ሁለት አይነት የፍትሐት ሥርአት ይደረጋሉ::

1ኛ-ጉዞ ፍትሐት :- ይህ ፍትሐት ለቤተክርስቲያን አገልጋዮች፣ለሊቃ ውንት ፣ለመምህራን ለባለሥልጣናት (ለነገሥታቱ) የሚደረግ ከ ከግማሽ ቀን በላይ የሚደርስ ሰዓት የሚፈጅ የጸሎት ሥርዓት ሲሆን ከሟቹ ቤት ተነሥቶ እስከ ቤተመቅደስ ድረስ የሚፈጸም ነው:: በዚህ የጸሎት (የጉዞ ፍትሐት) ደግሰው የሚያበሉ ሁሉ እንደተደ ረገላቸው በተለምዶ የሕግ ያህል ጸድቀዋል::

2ኛ- ተራ ፍትሐት:- ምንም እንኳ በጉዞ ፍትሐት ጊዜ ያለው የመሣርያው ፣የካህናት፣ ብዛ ትና ድምቀት በተራ ፍትሐቱ ጊዜ አንድነት ባይኖርም የሚጸለየውና የሚወረበው ቀለም ግን አንድ ሆኖ በነጠላ (በአጭር) የሚደረግ ፍትሐት ነው ::

ለሟቹ የሚጸለይለት የጸሎት አይነቶች

1 . ውዳሴ ማርያም
2. አንቀጸ ብርሃን
3. ወንጌለ ዮሐንስ
4. 15ቱ የነቢያት ጸሎት
5. 150 መዝሙራት
6. መስተብቁዕ

ሁሉንም የጸሎት አይነቶች ለሟቹ ሥርየትን ለማስገኘት እንደሚደገሙ የታወቀ ሲሆን ጎልቶ የሚታወቀው መዝሙረ ዳዊት ነው::

150 የሚሆነውን መዝሙረ ዳዊትን በመከፋፈል በአስከሬኑ ላይ ይጸለያል:: ጸሎቱ ከሟቹ ጉዳይ ጋር የማይገናኝ ከመሆኑ ባሻገር ሬሳውንና ቤተሰብን በመርገም በዘመዶቹ ሁሉ የስድብ መአት እንዲወርድባቸው የሚደረግ ሆኖ እናገኘዋለን ::

ጸሎቱ በግዕዝ ሆኖ ምዕመኑ እንዚል አቡነዘበሰማያት ሲሉ ተቀብሎ አሜን ይሁን ይደረግ ከማለት ያለፈ ምሥጢሩን የመረዳት እድል ባለመኖሩ እርግማኑ እንደ ኃጢአት ሥርዩት ተቆጥሮ ያለ የሌለን ንብረት እያሟጠጡ በመደገስ እርግማንን ተቀብሎ ይሄዳል ::

መዝሙረ ዳዊት ለሟቾች የኃጢአት ሥርየት እንዲያመጣ የተጻፈ ጸሎት ሳይሆን አማኝ በሕይወተ ሥጋ ሳለ አንብቦ አስነብቦ ተረድቶ እርሱን የሚመለከተውን ሕግ የሚጠብቅበት በመከራው እንዲጽናናበት የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲያውቅበት ለትምህርት የተጻፈ ድርሰት ነው::

ገበዘ መቅደስ የሆኑቱ የእኛዎቹ ግን ይህን 150 መዝሙር በላዩ ላይ ስንጮህበት ኃጢአቱ ይሰረይለታል ይሉናል እስኪ ከሚጸለየው ጸሎተ ዳዊት እንይ:-

መዝሙር 51

« ሁል ጊዜ በመተላለፍ እንደበትህ ኃጢአትን ያስባል
. እንደተሳለ ምላጭ ሽንገላን አበዛህ

. ከመልካም ይልቅ ክፋትን
. ጽድቅን ከመናገር ይልቅ ዓመፃን ወደድህ
. የሚጠፋ ቃልን ሁሉ የሽንገላን ምላስ ሁሉ ወደድህ
. ስለዚህም እግዚአብሔር ለዘላለም ያፈርስሃል
. ከቤትህም ይነቅልሃል ያፈልስህማል

መቼም ማንም ፍትሐት የተደረገለት ሰው ይህን ውርጅብኝ ሰምቶ አያውቅ ይሆናል ለምን ቢሉ የምናዜመው በግእዝ የምናነበው በግእዝ ነውና ከምዕምናን ጆሮ የራቀ ነው።

እስኪልብ በሉ የሞተን ሰው አስከሬኑን ከፊት ለፊት አስቀምጦ ይህ ሲጮህበት ምሕርት እየለመኑለት ነው ብሎ ቤተሰብ አሜን አሜን ይላል። ይህ ብቻ አይደለም የባሰውን እንመልከት :- መዝ108/109፣6-9

... በላዩ ኃጢያተኛ ይቁም
በተሟገተ ጊዜ ተረቶይወጣ
ጸሎቱም ኃጢያት ትሁንበት
ዘመኖቹ ጥቂት ይሁኑ
ሹመቱን ሌላ ይውሰዳት
ልጆቹም ድኃ አደግ ይሁኑ
ሚስቱም መበለት ትሁን።
ልጆቹም ተናውጠው ይቅበዝበዙ ይለምኑም
ከሥፍራቸው ይባረሩ
ባለ እዳም ያለውን ይበርብረው
እንግዶች ድካሙን ሁሉ ይበዝብዙት
የሚያግዘው አይገኝ
ለድኃ አደግ ልጆቹ የሚራራ አይኑር
ልጆቹም ይጥፉ
በአንድ ትውልድ ስሙ ይደምሰስ
የአባቶቹ ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ይታሰብ
የእናቱም ኃጢአት አትደምሰስ
በእግዚአብሔር ፊት ይኑር

የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ የሟቹን ኃጢአት ለማስተስረይ ለቀብር የመጣውን ከ1000 - 2000 የሚደርሰውን የዋህ ሕዝብ አቁመው በግእዝ

በተሸፈነ ሥርአት ራሱንና ቤተሰቡን በመርገም ቆይተው ይምሐረነ ወይሣሃለነ በሚል ማደናገሪያ ሕዝቡን ይሸኙታል ፡፡

በእርግጥ ከጥቂቶች በስተቀር አብዛኞቹ ካህናቶቻችን ዜማና ንባቡን በልምድ ጸሎቱን ያድርሱ እንጂ ምን እንደተናገሩ ምን እንደጸለዩ ግንዛቤ የላቸውም ከመካከላቸው አንዱ እንኳን በሟቹ ላይ ለምን እንዲህ እንደሚጸልዩ ራሱንም ሆነ ጓደኞቹን የጠየቀ የለም፡፡

ታዲያ ይህ የፍትሐት ጸሎት ሥርዬተ ኃጢአት እያስተሰረየ ነው ወይስ እርግማን እያስተላለፈ ? ምእመናንስ ምን እንደተባለ ሳናውቅ ዝም ብለን አሜን በማለት መኖሩ ሁለት ጉዳት ነውና መንቃት አያስፈልግም ትላላችሁ ?

እውነተኛ ክርስቲያን በሕይወተ ሥጋ ሳለ በክርስቶስ አምኖ ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቆ በሥጋ ዘመኑም ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ይቅርታ እየጠየቀ እየተናዘዘ ዕለት ዕለት ኀብረቱን ከእግዚአብሔር ጋር እያስተካከለ በመኖር ሲሞት ወደሚወደው አምላኩ ወደ እግዚአብሔር እንደሚሄድ ተረድቶ ይኖራል እንጂ በፍትሐትና በድግስ ጋጋታ የኃጢአት ሥርዬት እንደማይገኝ መረዳት ይኖርበታል ፡፡

«ሕዝቤ እውቀትን ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቷል፡፡»(ሆሴ1:4 - 6) እንዲሁም ሕዝቤ ሆይ የመሯችሁ አስተዋችኋል እንደተባለው ሆኖብን ይሆን? (ኢሳ3:12)

<u>*ታዲያ ሰው የሚጸድቀው እንዴት ይሆን ?*</u>

እግዚአብሔር ለዓለም ሁሉ መድኃኒት አድርጎ በላከልን በመድኃ ኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው .. በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለምን ወዶአልና /ዮሐ3 ÷16 / .. እውነት እላችዋለሁ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው » / ዮሐ6÷ 47/

«የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ወደእኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚ ያምን ሁልጊዜ አይጠማም » / ዮሐ 6÷47/

እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ቅድስት ከምትሆን ከድንግል ማርያም በሥጋ በመወለዱ ለኃጢአታችን ሥርየት ቅዱስ መሥዋዕት /በግ ሆኖ/ በእግዚአብሔር ፊት አስታራቂ (ካህን ሆኖ) ለእምነታችን አስተማሪ (ሐዋርያ ሆኖ) የተሟላ

ደኅንነት እንድናገኝ አድርጎናል:: ሐዋርያቱም « ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘየአትት ኃጢአተ ዓለም » በማለት በግነቱን መስክረዋል:: ( ዮሐ 1÷29 )

« እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናት ሠራዬ ኃጢያት ወደምሳሴ አበሳ » ( ቅዳሴ) ትርጉም :- « ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአትን የሚያስተሰርይ ሊቀ ካህናት » በማለት ኃጢአት የሚያስተሰርይ ካህን መሆኑን እንዲሁም « ርእይዎ ለዝንቱ ሐዋር ያክሙ ሊቀካህናት ዘኪያሁ ትትአመኑ ኢየሱስ ክርስቶስ » ብለው የሃይማኖታችንን ሐዋርያነቱንና ሊቀ ካህናትነቱን /ዕብ 3-1/ ገልጠዋል::

በተለይ ቅዱስ ዮሐንስ «ወንሕነኒ ርኢነ ወሰማዕነ ከመ አብ ፈነወ ወልዶ መድኅኔዓለም» ትርጉም:- እኛም አይተናል አብ ልጁን የዓለም መድኃኒት እንዲሆን እንደላከው » በማለት የምንድንበትን የመዳኛ መንገድ እርሱ እንደሆነ አሳይተዋል / ዮሐ 4 ÷14/

በፍትሐትና በድግስ በሌሎችም መንገዶች ደኅንነት እንደማይገኝ ሲያስረዱም « ወአልቦ ካልእ ስም በታሕተ ሰማይ ዘይትወሀብ ለእጓለ እመ ሕያው በዘ የሐዩ » ትርጉም « መዳን በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለም » ( የሐዋ 4÷ 12 ) መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም « <u>አነ ውእቱ ፍኖትኒ ወጽድቅ ወሕይወት ወአልቦ ዘይመጽእ ኀበ አብ ዘእንበለ እንተ ኀቤየ »</u> ትርጉም « <u>እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም »</u> ብሏል:: (ዮሐ 14÷6 )

መድኅን ክርስቶስ በዮሐ 10÷ 1 ላይ « <u>ዘኢቦአ እንተ አንቀጽ ውስተ ዐጸደ አባግዕ ... ሰራቂ ውእቱ ወጉሕልያ »</u> ትርጉም « <u>ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባ እርሱ ሌባ ነው ወንበዴም ነው »</u> በማለት ለመጽደቅ ሆነ ለሥርዬተ ኃጢአት ሌላ መንገድ ፈላጊዎችን ይገስጻል::

እንግዲያውስ በጸሎተ ፍትሐት ኃጢአት እናስተሰርያለን የሚሉትም ሆነ እንዲሰረይላቸው አስከሬን አቅራቢዎች ከዚህ ግብር ሊታረሙ ይገባል:: እግዚአብሔር የመረጠውንና ያለውን ትተን ለምን ሰዎች በፈጠሩት ገመድ እንታሰራለን ?

ሰው የሚጸድቀው የጌታ ቃል እንደሚለው በሕይወት ዘመኑ ከጌታችን ጋር በመስማማትና ከኃጢአት እየራቀ በመኖር፣ በሥጋ ድካም በሰይጣንና በዚህ ዓለም ተጽእኖ በሕይወቱ ኃጢ አት ቢያልፍ ወይም ቢያደርግ ኃጢአት የለብኝም ሳይል ከአመጻ ሥራ እንኳ ሊያነጻውና ሊታደገው ወደሚችል ወደታመነው ሊቀ ካህናትና ጠበቃ እንዲሁም አራቂ እግዚአብሔር ወሰብእ ወደ ሆነው ወደ አምላካችንና መድኃኒታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ በመቅረብ ሥርዬተ ኃጢአቱን ሊያገኝ ይችላል እንጂ ሌላ መንገድ ሆነ ምክንያት የሌለው መሆኑን ሊገነዘብ ይገባል። (1ዮሐ 1÷ 1- 10 ፣ 2÷ 1- 2 ዕብ 2÷ 16 - 18) አፈታለሁ ብሎ መርገም አስፈታለሁ ብሎ ማስረገም ከእኛ ይራቅ።

## ለመስቀልና ለማርያም የሥላሴ ክብር ይገባቸዋል

በቤተክርስቲያናችን የነበሩት ጸሐፊዎች በእጃቸው የወደቀውን የዋሕ ሕዝብ ወደ ፈለጉት አቅጣጫ ለመውሰድ በተሞሉበት መንፈስ /ርካሽ/ በመነዳት ያሻቸውንና ደስ ያላቸውን መጻፍ መናገር ተቃዋሚ የማይገኝለት መብታቸው አድርገው የተቀበሉት ነው።

አንድነትን በሦስትነት ሦስትነትን በአንድነት ሳትለያት ሳትደባልቅ የምታምነውን ቤተክርስቲያን መቅደስ /የጸሎት ቤት/ ምሽግ አድርገው ከዚያም በመነሳት በዚሁ መንፈሳዊ ካባ ተሸፍነው እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል ቅዱሳን እንዲህ ነግረውናል ወ.ዘ.ተ በማለት ጸሐፍቱ የመንፈሳዊ ትምህርት እውቀት የሌለውን ሕዝባችንን ቀርቶ ሊቅ መምህር የተባሉትን ሁሉ በነገር ከታባቸው ማርከው የትምህርታቸው አስተናገጅ አድርገዋቸው ነበር።

ጸሐፊ ድርሳን ወገድል ወተአምር የሆኑት እነዚያ ሰዎች እንደ እግዚአብሔር «ንግበር»( እንፍጠር ) ማለት ለእነርሱ ቀላል በመሆኑ እርሱ /እግዚአብሔር ያልሠራውን ያልፈጠረውን ነገር በጽሑፋቸው መፍጠር ተግባራቸው ነው።

ጸሐፍቱ ሰኞን ረቡዕ ሆኗል ማለት ከፈለጉ ረቡዕ ያደርጉታል ጨለማውን ብርሃን ነው ካሉም ይታመናሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ፈጽሞ ያልተገለጠና መነሻ የሌለውን ታሪክ መጽሐፍ ሲፈልጉ ማቴዎስ ረስቶት ነው ሉቃስ ዘንግቶት ነው ቢሉም ይሆንላቸዋል።

እንደምሳሌ ብንወስድ ተአምረ ኢየሱስ የሚባል መጽሐፍ ተጽፎ በሰፊው በገበያ ላይ ይገኛል:: የመጽሐፉ አዘጋጅ ለመላው ዓለም ምዕመናን የዘላለም የሕይወት ምግብ አዘጋጅና አከፋፋይ ነኝ ያሉ ሰው ናቸው::

ሰውየው ከቤተክርስቲያናችን ገዳማትና አድባራት ውስጥ ከሚገኙ መጻሕፍት ጋር አመሳክረው (በእርሳቸው አባባል አሪጅናሉ አለ) ለምዕመናን አዝነው በ95 ዓመታቸው ጽፈው እንዳበረከቱ በመጽሐፋቸው መግለጫ በሚለው አንቀጽ ጽፈዋል::

መጻሕፍት የሚጻፉት ያው በሃይማኖት ሽፋን በመሆኑ ሰውየው በጻፉት በዚህ ተአምረ ኢየሱስ ውስጥም ከመጽሐፍ ቅዱስ የተቀዱ እውነተኛ የሆኑ ታሪኮች ይገኙበታል:: ይህም ማደናገሪያ ሲሆን ዓላማቸው እግዚአብሔር ያላለውን ያልተናገረውን በመጨመር ሕዝቡን በበደል ማስያዝ ስለሆነ እንዲህ የሚል ተረት አስገብተውበታል::

« እስመ አልቦ ነገር » በምትለው ፊሊጥ ጻድቅ ዕገሌ በአንዲት ቀን ስንዴ ዘርተው አፍርቶ አበራይተው አስፈጭተው አቡክተው ጋግረው ለቅዳሴ ጊዜ ቅዱስ ቁርባን /የጌታ ራት/ አዘጋጅተዋል እንዴት ሲባሉ ለእግዚአብሔር ምን ይሳነዋል በማለት አማኝ ይመስላሉ::

ለእግዚአብሔር ቅንጣት ታህል የማይችለው አለ ብለን አናስብም እርሱ «ከሃሊ ኩሉ» ነውና:: ግና ያላሳየንን አየን ያልተናገረንን ተናገረን ብንል እግዚአብሔርን ማክበር ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ መቀለድ ይሆናል:: (ሮሜ 3: 5 - 6 ) በብሉይ ኪዳን ከነበሩት ነቢያት አንዳንዶቹ የተናቁበት አንዱ ምክንያት ያልተናገረውን ቃል የሚናገሩ ወይም ከልባቸው አፍልቀው የሚያወሩ በመሆናቸው እንደሆነ ቅዱስ ቃሉ ያስረዳናል (ኤር 14 ÷ 14 18

በዚህ በተአምረ ኢየሱስም እንዲህ ያለ ነገር ተጽፎ ይገኛል:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለጌታችን ስለመድኃኒታችን ስለኢየሱስ ክርስቶስ እናውቅ ዘንድ የሚገባንን ብቻ እንድናውቅ ፈቀደ እንጂ ገና ያላወቅነው ነገር እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ « በድንግዝግዝ እንደማይ ነኝ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ » በማለት ተናግሯል::

ለምሳሌ ልደቱ በበረት እንደተወለደ እንጂ የድንግል ማርያም የአወላለድ ሁኔታ አልተገለጠልንም እንበለ ሕማም ወጻእር ይሁን አይሁን አልተጻፈም ይህም ለእኛ አልተነገረም:: ግዝረቱ ለእግዚአነ እንደልማዳቸው በ8 ቀኑ ወደ

ቤተመቅደስ እንዲወስዱት እንጂ እንዴት ሥርዓቱ እንደተፈጸመ ለእኛ አልተጻፈም:: ጥምቀቱ በእደ ዮሐንስ በማየ ዮርዳኖስ እንደተጠመቀ እንጂ ዮሐንስ እንዴት እንዳጠመቀው ምን እያለ እንደተናገረ እንዴትስ እንደነበር በዝርዝር የተጻፈ ነገር የለንም::

በተለይ ከ12 ዓመቱ - 30 ዓመቱ የት እንደኖረና ምን እያደረገ እንደነበር ለምን ታሪኩ እንዳልተዘገበ ለእኛ አልተገለጠም መጽሐፍ አምናችሁ ትድኑ ዘንድ ይህ ተጽፏል በማለት ሲናገር እነዚህ ከላይ ያልናቸው ጥያቄዎች ባይገቡንም እንኳ ሰው ለደህንነት የሚያበቃው መልእክት በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ምሪት ተጽፎልናል ማለት ነው::

ብዙዎች የፈላስፋዎችን ጥያቄ ለመመለስ ታሪክ አጥንተናል አይሁድን ጠይቀናል በማለት መላምት የሆኑ ምላሾችን በመጨመር ለመጻፍ ቢሞክሩም በተጻፈው ላይ አትጨምር ባለው ሕግ መሠረት ውድቅ ይሆንባቸዋል::

ጌታችን በቤተመቅደስ ከታየበት ከ12 ዓመቱ ጀምሮ በጥምቀት ጊዜ እስከተገለጠበት 30 ዓመቱ የት ነበር ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ከሐዲያን ሩቅ ምሥራቅ ሄዶ እንደነበር በዚህም ጽሑፍ ለመናገር የሚቀፈውን አስነዋሪ ነገር እንደጻፉበት የቅርብ ዘመን ትውስታ ነው:: ሐዋርያትና የተኳቸው አበው ቅዱሳን ከተጻፈልን ውጪ ሌላ ሳይጨመር የተቀበሉትን ብቻ ለእኛ አስተላለፉልን የሚጠቅመንም እርሱ ብቻ ነበርና::

የሀገራችንም ጸሐፊዎች እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ያልገለጣቸውን የጌታችን በሥጋ የሕይወት ዓመታት እኛ አግኝተናቸዋል በሚል ፈሊጥ እንዲህ ጽፈውልናል:: በመጽሐፉ 14ኛ ተአምር ጌታችን የ5 ዓመት ልጅ ሳለ በጭቃ 12 ወፎችን ሠርቶ እፍ ሲልባቸው እንደበረሩ ወፎችም እግዚአብሔርን እንዳመሰገኑ ( ይህንኑ ታሪክ በቁርዓን ———— ተመልከት)

እንዲሁም በ16ኛ ተአምር የ5 ዓመቱን ኢየሱስን አንድ ልጅ ተነስቶ ደረቱን በመታው ጊዜ ኢየሱስ ልጁን እንደረገመውና ልጁ ወድቆ እንደሞተ ( ይህም ከክብሩ የመጣበትን ዓላማ ለመበረዝ የታቀደ ነው) የወጉትን እንኳ አባ ሥረይ ሎሙ እስመ በዘኢየአምሩ ይገብሩ ... የሚያደርጉትን አያውቁምና አባት ሆይ ይቅር በላቸው ነበር ያለው :

ሐዋርያት ስለጌታችን ሲጽፉ « ብርዐ ቅጥቁጠ ኢይሰብር ወሱዐ ዘይጠይስ ኢያጠፍዕ » የተቀጠቀጠ ሸንበቆን አይሰብርም የሚጤስ ጧፍን አያጠፋም » ነበር ያሉት ( ማቴ 12: 21 )

ያልተጻፈ በመጻፍ የተካኑት የእኛዎቹ ጸሐፊዎች ለጆር የሚሰቀጥጥ በተለይም ልዑልና ክቡር ተወዳዳሪ የሌለውን እግዚአብሔር ለሚያመልኩ ክርስቲያኖች የሚያሳዝን ቃልን በድፍረት ጽፈዋል፡

የምናመልከው ሦስትነት ያለው አንዱ አምላካችንን የሚመስል የሚተካከል ሌላ መጨመር አለበት አሉ ። እንዴትና እነማን ተብለው ሲጠየቁ ለእሉ ክልዔቱ ፍጡራን እነዚህ ሁለቱ ፍጡራን ማለትም መስቀለኛ እንጨት /መስቀል/ እና ማርያም የፈጣሪ ክብር ይገባቸዋል ከፈጣሪም ጋር በክብር እኩል ሆነዋልና በማለት ጽፈዋል፡

የካህናቱን ድምፅ ብቻ ሰምቶ አሜን የሚለውም ሕዝባችን ከመስማማት በቀር አማራጭ የሌለው በመሆኑ እነሆ መጽሐፍን አሜን ይሁንልን ይደረግልን በማለት እየተሳለመው ይወጣል ይገባል። ለእነዚህ ሁለቱ ፍጡራን መስቀሉና /እንጨቱና/ ማርያም ከሥላሴ ጋር በክብር ከተካከሉ የፈጣሪም ክብር የሚገባቸው ከሆነ አምላካችን አንድም አምስትም ሊሆን አይደለምን?

በሥላሴ ትምህርታችን በክብር በሕልውና በመለኮት አንድ የሆኑ ሦስት አካላት የሚለውስ ሊፋለስ አይደለምን መናፍቃን ምን ያህል
በክህደት እንደሰለጠኑ ያሳየናል።
ከዚህ የተነሣ ስብሐት ለእግዚአብሔር ተብሎ
ወለወላዲቱ ድንግል
ወለመስቀሉ ክቡር እየተባለ ይዘመራል ይጻፋል
ይህም ማለት ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል ብሎ በዚሁ ምስጋና
ለማርያምም
ለመስቀልም ይገባዋል ተብሎ ይተረጐማል።

እንደ እኛዎቹ ጸሐፍት አባባል ጌታችን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ ማለቱ ተሳስቷል መስቀልንና ማርያምን ከፈጣሪነት ክብር አጉድሏቸዋልና ፡ ( ማቴ 28÷ 19 - 20 ) ሐዋርያት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር የእግዚአብሔር ጸጋ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከእናንተ ጋር ይሁን ሲሉ አሁንም ማርያምንና መስቀልን ለይቶ አስቀርቷልና ተሳስቷል ማለት ነው ፡ 1ኛ ቆሮ 13÷14 )

ለመሆኑ ከልዑል አምላክ ጋር በክብር የሚተካከል ክብርንም የሚቀበል ሌላ ማን ነው ? ሰይጣን የወደቀው በልዑል ክብር እመስላለሁ በማለቱ አይደለምን

? እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም :ራሱ እግዚአብሔር እንዳለ እኔ እግዚአብሔር ክብሬን ለሌላ ለማንም አልሰጥም ( ኢሳ 42 ÷ 8 )

በተለይም በኢሳ 44 ÷ 6 - 7 እኔ ፊተኛ ነኝ እኔ ኋለኛ ነኝ ከእኔ ሌላ አምላክ የለም እንደኔ ያለ ማን ነው? አነሰ ተብሎ የማይጨመርበት በዝቷል ተብሎ የማይቀነስ ሦስትነት ካለው አንድ አምላክ ውጪ ሌላ እርሱ ማን ነው? ጸሐፊዎቻችን ይሁኑ ያሏቸው ሁለቱ ፍጡራን ቅዠት እንጂ ከፈጣሪ ጋር የሚተካከሉ አይደሉም::

## የታምርህን መጽሐፍ ዝታ /ቨሩን/ የተሳለ 80 ዓመት ሙሉ የሠራው ኃጢአቱ ይሰረይለታል

በኢትዮጵያ የክርስትና ታሪክ ውስጥ የሕይወት ወንጌልን በመስበክ ስመ ጥር የነበረውንና የመጀመሪያው ሊቀ ጳጳስ ሆኖ የተሾመውን የሃይማኖት አባት ፍሬምናጦስን በኋላም /ከሣቴ ብርሃን የተባለውን/ ሰው ስምና ታሪክ ለማጉደፍ እንዲሁም ዛሬ በቤተክርስቲያናችን የታጐሩትን ከንቱ መጻሕፍት ከጥንት ጀምረው ነበሩ ለማለት እንዲያመቻቸው «ተአምረ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን» በማለት በጻፉት ጽሑፍ የተለመደውን የክሕደት ጽሑፍ አስፍረዋል::

መቼም አልቦ ዘይሰአኖ ለእግዚአብሔር የሚለውን ጥቅስ እየነጠቁ በመለጠፍ እግዚአብሔር የ10 ሣንቲም ዳቦ የሰጠውን ለቤተክርስቲያን ማሰሪያ አንዲት ድንጋይ የተሸከመውን የዘላለም ሕይወትን ይሰጠዋል ሲአልንም አያሳየውም የሚለውን ክህደት ለማስጠበቂያ የሚናገሩት ጓደኞች ደራሲዎች የከሣቴ ብርሃን አቡነ ሰላማ ተአምር ይህ ነው ብለው የጻፉትን እንይ ::

በነዚያው መጻሕፍቶቻቸው እንደሚገለጠው ለሞት ተቃረበ ያሉትን ሰው ሁሉ ቅድስናውን ብቃቱን ለማሳየት እንዲህ ይላሉ ዕገሌ የተባለው ጻድቅ /ቅዱስ/ ለሞት በተቃረበ ጊዜ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሦስትነቱ /ሥላሴ/ ከቅዱሳን መላእክት ጋር በኪሩቤል በሱራፌል ላይ ሆኖ እልፍ አዕላፍ መላእክት በግራው እልፍ አዕላፍ መላእክት በቀኙ ሆነው እየበረረ ይመጣል ይላል :

መቼም ሁል ጊዜ በየቤተክርስቲያኑ ደጃፍ የቀበርናቸውን ሰዎች ሁኔታ ስንመለከት እንኳንስ ጌታና መላእክት ወይም ሥላሴ መጥተው ሊስሙት

ሊዳስሱት ቀርቶ እድርተኛ እንኳ ደመቅ ያላለበት የቀብር ሥርዓት እንዳሳለፍን የሚረዳ ቅዱስ ጻድቅ እያሉ የጠሯቸውን ሰዎች የቀብር ሥነ-ሥርዓት ተአምረኛ በማድረግ እየጻፉ የዋሁ ያለ ተቃወሞ እንዲህ ከሆነ በማለት ለማቾቹ ይገዛል በማቾቹ ይማጸናል።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስረዳን ደጋጉ ሐዋርያት መምህራን በዚያ በመከራው ጊዜ ሲያልፍ በአንደኛው የቀብር ሥነ-ሥርዓት ላይ ሥላሴ ነበሩ የሚል የተገለጸ ጽሑፍ የለም።የእኛዎቹ ግን ቅዱሳን እያሉ በሚጠሯቸው ሰዎች ሞትና ቀብር ላይ መገኘት ብቻ ሳይሆን ጌታችን እግዚአብሔር የማቹን ከንፈር ሳመው በማለት ነውር ነገር በእግዚአብሔር ላይ ይናገራሉ።

ጸሐፊዎቹ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የሚያርፍበት ሰዓት በደረሰ ጊዜ ጌታችን ወደ እርሱ መጥቶ ሞቱን ባበሠረው ጊዜ አቡነ ሰላማ ጌታችንን እንዲህ አለው የሚል ፈጠራ ጽፈዋል « መታሰቢያየን ለሚያደርጉ ኃጥአንን ትምርልኝ ዘንድ እለምንሃለሁ። አንተ በሰጠኸኝ ቃል ኪዳን እነሱን ስሜን የሚጠሩትን ትምርልኝ ዘንድ እለምንሃለሁ አለው ይላሉ።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጥንተ አመሠራረቷ በእውነት ወንጌል ላይ ነው የሚለውን ታሪክ በማጉደፍ ቀደሞውንም በዝክርና በተዝካር በሟች ሰዎች ጸሎትና ምልጃ የተመሠረተች ቤተክርስቲያን ናት ለማሰኘት መናፍቃን የጻፉት እንጂ ከሣቴ ብርሃን ሰላማ ይህን እንዳለ የሚያረጋግጥ የተጨበጠ ታሪክ የለንም።

መናፍቃኑ እንደተለመደው መታሰቢያዬን የሚያደርጉ በሚሉት ሐረጋቸው በሟች ሰዎች ስም የሚደረገውን የድሆች ቤት ብዝበዛ በብዙ መረጃ ለማስረገጥ እንዲሁም ከጥንት ጀምሮ የነበረ ነው ለማሰኘት የተደረገ እንጂ በማንም ተዝካር /መታሰቢያ/ ጸበል ጸዲቅ እየተባለ በሚደረግ ድግስ እግዚአብሔር የዘላለም ሕይወት እሰጣለሁ አላለም። «በእርሱ የሚያምን» አለ እንጅ ።

ስሜን ለሚጠሩ የሚለው የመናፍቃኑ ወንጀል የጽሑፍ ሥሕተት ያለመረዳት ውጤት ሳይሆን ብዙ ጊዜ እንዳልነው የእግዚአብሔር ስም ከሕዝቡ ኅሊና እንዲሰረዝ የሰይጣንን ዓላማ ማስፈጸም ነው።

መጽሐፍ « እስመ ኩሉ ዘጸውዐ ስመ እግዚአብሔር የሐዩ » የጌታን ስም የሚጠራ እርሱ ይድናል / ሮሜ 10 : 13 ) የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ

ሁሉ ይድናል ( ኢዩ 2: 28 -32 ) አለ እንጂ የዕገሌንና የዕገሊትን ስም የጠራ ኃጢአቱ እንዲሠረይለት ቃል ኪዳን አልገባም::

ሐዋርያው ጳውሎስ በቆርንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ የየራሳቸው ቅዱሳን የሚሏቸውን ሰዎች እየመረጡ ሲሄደኑ አይቶ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን ጳወሎስ ስለ እናንተ ተሰቀለን ኬፋስ ዮሐንስስ ምንድር ናቸው? በማለት ነቅፎ የአንድ እንኳ አገልጋይ ስም እንዲጠራ እንዳልተፈቀደ ገልጧል ( 1ኛ ቆሮ 1+10 15 )

መልካም ምግባራቸውን በማስታወስ ሆነ መጥፎ ግብራቸውን በመዘከር ጳውሎስ እንዲህ አለ ይሁዳ እንዲህ አደረገ በማለት ለትምህርት እንጥራቸው እንጂ የዘላለም ሕይወት ለማግኘት ምህረት ለመቀበል የጳውሎስን የጴጥሮስን የጊዮርጊስን ሆነ የተክልዬን፣ የአቡዬን ሆነ የክርስቶስ ሠምራን ስም እየጠሩ ጽድቅ፣ የዘላለም ሕይወት አገኛለሁ ብሎ ማሰብ አምልኮ ባዕድ ነው::

ጌታችን በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 5: 43 ላይ ስለዚህ ሲናገር :-

«<u>አነ መጻእኩ በስመ አቡየ ወኢተወከፍክሙኒ ወእመ</u>
<u>መጽአ ካልእ በስመ ዚአሁ ኪያሁ ትትዌከፉ »</u>
« <u>እኔ በአባቴ ስም መጣሁ አልተቀበላችሁኝም ሌላው</u>
<u>በራሱ ስም ቢመጣ እርሱን ትቀበሉታላችሁ »</u>

እንዳለው ሆኖብን በአባቱ ስም የመጣውን ጌታ በመተው ለጽድቅና ለምህረት እኛ ቅዱስ እያልን የሾምነውን ሰው ስምና መታሰቢያ እየተማፀንን እንገኛለን::

በመሠረቱ እውተኛቹ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ይህን የመናፍቃኑን ሤራ አይቀበሉትም መናፍቃኑ በማርያም በመላእክት በሌሎችም ሰዎች ስም እየተጠቀሙ የሚጽፏቸው ወንጀሎች በሙሉ የእግዚአብሔር ሰዎች የሚደግፉት አይደለም::

በሰዎች መታሰቢያና ስም ጽድቅ ሆነ ምህረት ቢኖር ኖሮ ያን ያህል መከራ የተቀበለው ሐዋርያው ጳውሎስ በስሜ እንዲህ አድርጉ ባለን ነበር እርሱ ግን« ወኩሎ ዘትገብሩ በስመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ግበሩ» ማለትም «የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አድርጉት ( ቆላ 3: 17 አለ : የተረት መጽሐፉ ይቀጥልና :-

- ጌታችንም ልመናውን ሰምቶ « መታሰቢያህን ያደረገ የጠራ በጸሎትህ የታመነውን ቤተክርስቲያንህን ያሳነጸውን እስከ 15 ትውልድ ድረስ ከገሃነመ እሳት አድነዋለሁ አለው»

መቼም ደራሲዎች የቃል ኪዳኑን ውርርስ የዘር ሐረግ በ10 በ15 ትውልድ እምረዋለሁ ብሏል የሚሏት አንቀጽ ጽድቅ የናፈቀውን ሕዝብ እስከ 15 ትውልድ ሊያረሰርስ የሚችል ቃል ኪዳን አለን ብለው ለማጃጃል ነው::

15 ትውልድ የትውልድ ዕድሜ በመጽሐፍ ቅዱስ

ሀ. 40 ዓመት (40 ዓመት አንድ ትውልድ ተቆጣሁ ይላልና) በዚህ ስሌት መሠረት :-

40 ዓመት × 15ትውልድ = 600 ዓመት

ለ. 70 ና 80 (የሰው ዕድሜ ግፋ ቢል ሰባ አልያም ሰማንያ ነው ይላልና(መዝ 89:10 ) በዚህ ስሌት 80 x 15 = 1200 ዓመት

ወይም 70 x 15 = 1050 ዓመት

ሐ. 100 ( አንድ ትውልድ እየተባለ ይነገራልና ) በዚህ ስሌት :-

100 × 15 = 1500 ዓመት

እንግዲህ የገድልና የድርሳን የተአምርም ጸሐፊዎች ዕገሌ በተባለው ወይም በተባለች ጻድቅ ስም በሚደረግ ድግስ 10 ና 15
ትውልድ እንዲማር በተናገሩት መሠረት ደጋሹ ከላይ በተገለጸው ስሌት ሕግ :-

ሀ. በተራ ቁጥር አንድ እንደተገለጠው ከሆነ እርሱና በስድስት መቶ ዓመት ውስጥ ያሉ ዘመዶቹ

ለ. በተራ ቁጥር ሁለት እንደተገለጠው ከሆነ ደግሞ እርሱና በ1200 ዓመታት መካከል ያሉ ዘመዶቹ

ሐ. በተራ ቁጥር ሦስት እንደተገለጠው ደግሞ እርሱና በ1500 ዓመታት መካከል የሚኖሩ ዘመዶቹ ሁሉ የደኅንነት ዋስትናቸው የተጠበቀላቸው መሆኑን ያስረዳል::

ለነገሩ ሌላ ደጋሽ በመካከል የተነሳ ከሆነ ይህን የሚያህል ዓመት ዕድሜ ሊያራዝም እንደሚቻል መገመት አያዳግትም:: ምን ያህል ጸረ ወንጌል ትምህርት ቤተክርስቲያናችንን እንደወረራትና መናፍቃኑ ምን ያህል ይህን ሕዝብ አሥረው እንደያዙት ያስረዳል:

# ሩፋኤልና ሐዋርያት

መቼም የፈጠራ ቋታቸው ነጥፎባቸው የማያውቁት ቤተመቅደሱን ተተግነው እየኖሩ መንገደ ክርስቶስን ዱካ ሐዋርያትን እያጠፉ የነበሩት የእኛ ዎቹ ሰዎች በየጊዜውና በየሰዓቱ ለዓላማቸው ማሳኪያ የሚሆነን የፈጠራ ተረትና ኩሸት በየትኛው ጊዜ ይሁን በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ይገኙ ከመጻፍ ከመደጎስ የሚከለክላቸው አንዳች ነገር እንዳልነበር ዛሬ አቃጥለን እንኳ ቢሆን የማንጨርሳቸው የጉድ ጽሑፎቻቸው በብራና በወረቀት በጨርቅና በሰው ልብ በድንጋይና በእንጨት ጽላት ላይ ተጽፈው ለመከራ የዳረጉን ዕዳዎቻችን ምሥክር ናቸው::

እንዳሉት የሚሆንን ሕዝብ ጊዜና ክፉ ጉልበታቸው ስለሰጣቸው ያሹትን ቢጽፉ ቢናገሩ ቢደሰኩሩ ዕልል አሜን ከሚባለው ምላሽ በቀር የጠነከረ ተቃውሞ አጋጥሟቸው የማይውቅ በመሆኑ ለጽሑፋቸው ቅንጣት ታህል ጸጸት በሌለው ልባቸው በሕዝቡ ትከሻ ላይ ጭነውበት ኖረዋል::

ነገር ግን ጊዜ ደረሰ የተፈራው የተከበረውና አንቱ የተሰኘ ውሸት የሚፈርስ የሚዋረድበት ከተሰቀሉበት ቆጥ ወርደው ሥፍራ ለከበረው የጌታ ቃል ሊለቁ ዳግመኛ እኛ ብለው ላይናገሩ ምሳሌያቸው ሊጠፋ መታሰቢያቸው ሊደመሰስ ቃል ኪዳናቸው ሊፈርስ እግዚአብሔር ዘመንንና ትውልድን ላከ::

ተራ ከሆነው የክፉዎች ሤራ ተነሥተን የየዘመናቱን ክፋታቸውን ብናይ በሕዝባችን ልብና ኅሊና ሠርፆ የሚገኘው እነዚሁ ክፉዎች እየፈጠሩ የሰበኩት ከንቱና ለእግዚአብሔር መንግሥት የማይጠቅመው ተረት ተረት ነው:: ስለ ሰይጣንና ስለመላእክቱ ሲያስተምሩ ሔዋን 30 ልጆች ወልዳ 15ቱ መልክ ቀና 15ቱ ደግሞ መልከ ጥፉ ስለነበሩ እግዚአብሔር አንድ ቀን ወደ ሔዋን መጥቶ እስኪ ልጆችሽን ቢላት 15ቱን መልከ ቀናዎችን ደብቃ 15ቱን መልከ ጥፉዎችን ብቻ አቀረበችለት እርሱም ሌሎች የሉሽምን ? ቢላት የሉኝም ብላ ዋሸችው እርሱም የደበቀቻቸውን ሁሉ ረገመባት በዚያው መናፍስት ሆነው ቀሩ » በማለት በመስበካቸው ዛሬም እንኳ በአንዳንድ የቤተመቅደስ ሙያተኞች ስለሚነገር ሊታረም ያልቻለ እንቶ ፈንቶ ትምህርት ነው::

ይህም ብቻ አይደለም ድንግል ማርያም ጌታን በሕፃንነቱ ይዛ ወደ ግብጽ ስትሰደድ በመንገድ ላይ ውኃ አጠጡን ብላ የለመነቻቸው ሰዎች ስለተከፉባት በእቅፏ የያዘችው ጌታ ሰዎቹን በረገማቸው ጊዜ ጦጣና ዝንጀሮ እየሆኑ ገደል ገቡ በማለት ስነፍጥረትን እግዚአብሔር ሁለት ጊዜ እንደፈጠረ አስመስለው

ደግሞም ሁሉ እንደወገኑ ያውጣ የሚለውን ቃል ሽሮ የሰውን ዘር ዝንጀሮና ጦጣ አደረጋቸው ወደሚለው የሰነፎች ፍልስፍና ሊያስጠጉን ሞክረዋል ። ይህ ሁሉ የሚያሳየን ጸሐፊዎቻችን ለምን እንዴት መቼ የት የሚሉ ጥያቄዎችን ከዚህ ሕዝብ ባለማግኘታቸው እንደፈለጉት ለመሆን የነበራቸውን እድል የሚያሳይ ነው።

ድርሳነ ሩፋኤል እየተባለ በሚጠራ በፈጠራ ጽሑፍ ውጤታቸው ደግሞ እንዲህ የሚል ክህደትን አስፍረዋል። አንድ ቀን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያቱን ለወንጌል አገልግሎት ባርኮ በላካቸው ጊዜ ወንጌልን እንዲሰብኩ ብቻ ሳይሆን የድርሳኑ ጸሐፊዎች እነርሱ ሩፋኤል እያሉ የጠሩትን መልአክ ( እነርሱ እንዳሉት) ክብርና ገናናነት የስሙንም ትርጉም አውቀው ከወንጌሉ ጋር እንዲሰብኩት መፍቀዱንና ማዘዙን ጽፈዋል።

ከዚህ የተነሳ ሩፋኤል እያሉ የጠሩት መልአክ ሐዋርያትን ጠርቶ የስሙ ትርጓሜ የዋህና ሰውን አስደሳች ማዕረጉ 3ኛ ኃጢአተኞችን በኃጢአታቸው በእግዚአብሔር ፊት የማይከስ ይልቁንም ሰውን ከመውደዱ የተነሳ ኃጢአተኞች ንስሐ ይገቡ ዘንድ እድሜን በእድሜ ላይ የሚጨምር የ23 ነገደ መላእክት አለቃ የሆነ ሁልጊዜ ጳጉሜ 3 ቀን የሚከበር በዚህ ቀንም በእርሱ ስም መታሰቢያውን የሚያደርግ ሰው ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ማስገባት የሚችል መልአክ እንደሆነ ለሐዋርያት አስተማራቸው ሰበከላቸው።

በመጨረሻም በጸሐፊዎቹ ሩፋኤል የተባለው መልአክ የጌታ ተከታዮች የሆኑት ሐዋርያቱ ለተልእኮ በሚሄዱበት ሁሉ ያደርጉት ዘንድ ያላቸውን ሲናገር

<u>በግዕዙ</u>

« ኅሡ እምኔየ አ ሐዋርያት ኅሩያኒሁ ለእግዚአብሔር ኩሎ ጊዜ ከመ ዕቀብክሙ እስከ ትቀዉሙ ቅድመ እግዚአ ብሔር ወስብኩ ለኩሎሙ ሰብእ እለ ውስተ ኩሉ ዓለም ከመ ይግበሩ ተዝካርየ ወአነ እተነብል ኀበ እግዚአብሔር በእንቲአሆሙ ወአድኅኖሙ እምንዳ ቤሆሙ ወእምኩነኔ ለግሙራ ... »

<u>በአማርኛ</u>

እናንተ እግዚአብሔር የመረጣችሁ ሐዋርያት ሆይ በዚህ ዓለም ስብከተ ወንጌልን አስፋፍታችሁ ወደ እግዚአ ብሔር መንግሥት እስክትጠሩ ድረስ ሁል ጊዜ እጠብቃችሁና እራዳችሁ ዘንድ ከእኔ የምት ፈልጉትን ሁሉ ጠይቁ አሁንም በዚህ ዓለም ያሉ ሰዎች መታ ሰቢያን ያደርጉ ዘንድ አስተምሯቸው ስለእነ ርሱ ወደ እግዚአብሔር እየማለድሁ ከችግራ ቸውና ከጭንቀታቸው አድና ቸዋለሁ አላቸው

(ድርሳነ ሩፋኤል ዘጳጉሜን ቁጥር 29 )

= ለመሆኑ ይህን የሚያህል ጌታችን ራሱ ተሳትፎበታል የተባለውን ታሪክ ሐዋርያት እንዴት ሳያስተምሩት ሳይናገሩት አለፉ ያውም ለሌሎች ሰዎች እንዲያስተምሩ ታዝዘው

= ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያቱን ለተልእኮ ባርኮ ሲሸኛቸው « እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ደቀ መዝሙሬ አድርጓቸው ሲል ለሩፋኤልም መታሰቢያውን እንዲያደርጉ አስተምሩ ያላላቸው ለምንድን ነው ?

= ጸሐፊዎች እንዳሉት ሩፋኤል ሐዋርያቱን « ከእኔ የምትፈልጉትን ሁሉ ጠይቁ » ካላቸው በጽሑፋቸውና በትምህርታቸው ላይ ለምን ስሙን ሳይጠቅሱ በስሙ ሳይማጸኑ አለፉ ?

= ሩፋኤል መልአክ ስለመሆኑ ከሐዋርያት የቱን አስተምሯል ?

የጌታ ተከታዮች ሐዋርያት አንገታቸውን ለሰይፍ ሕይወታቸውን ሙሉ ለስቃይና ለመከራ አሳልፈው በመስጠት በጥም በረኃብ በእርዛት የሰበኩት ክርስቶስን እንጂ ሌላ እንግዳና ባዕድ ፍጡር አልያም አሉ የተባሉ መላእክትና ሰዎች ስምና ዝና አልያም የመታሰቢያ አከባበር ሆነ በእነርሱ ስም የሚደረግ ልመናና ምልጃ አልነበረም:: በእርግጥ በወቅቱ የነበሩ ፈላስፎች አዲስ አዲስ ነገር የሚወዱና ስለተለያዩ አማልክት እውቀትና አምልኮ የነበራቸው ቢሆንም የተወደዱት የጌታ ተከታዮች ግን « እኛስ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብከለን » እያሉ የስብከታቸውን ርዕስ ይናገሩ ነበር::

ጸሐፊ ድርሳን ወገድል የሆኑት አገር በቀል መናፍቃኑ ግን ጌታችን ራሱ ከወንጌሉ ጋር ሩፋኤል የተባለ ሰው ክብርና ዝና ገናናነትም እንዲሰበክ ሕዝቡም ሁሉ መታሰቢያውን እንዲያደርግ ሰበኩ ብሎ ለጥፋት ተልዕኮአቸው ተባባሪ አድርገው ቢያቀርቡትም እኛ እንላለን « ሐዋርያት ካስተማሩት ወንጌል የተለየ ወንጌል የሚሰብኩ ሁሉ የተረገሙ ይሁኑ » ( ገላ 1: 6 ) አሜን::

እንዲህ ዓይነቱ የፈጠራና የክህደት ጽሑፍ በቤተክርስቲያኒቱ የመጻሕፍት ታሪክ የጎላ ድርሻ አለው ተብሎ በሚነገርለት « ዲድስቅልያ » እየተባለ በሚጠራው መጽሐፍ ውስጥ ሳይቀር ገብቶ ጠርገን የማንጨርሰው የሚመስለን እዳ በሀገርና በሕዝብ ላይ አዝንበውብናል::

# ሰዶምን ያቃጠሏት ሐዋርያት ናቸው

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነበበው በሰዶምና በገሞራ ይኖሩ የነበሩት የሰው ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ባበዙት ኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር በዚያ የሚገኙትን ኃጢአተኞች ሊቀጣ የወሰነበትን ውሳኔ ለወዳጁ ለአብርሃም እንደነገረውና ወደከተማዋ የገቡት ሁለቱ መላእክት በዚያ ይኖር የነበረውን ሎጥን ከነቤተሰቡ በከተማዋ ላይ ሊደርስ ካለው ጥፋት ለማዳን በእግዚአብሔር እንደታዘዙት በአቅራቢያቸው ወደሚገኘው ተራራ በማሸሽ እንዳወጧቸው በዘፍ 18 ና 19 ላይ በግልጥ ሰፍሯል።

ሆኖም በእኛዎቹ ጸሐፊዎች ይህ በእግዚአብሔር መንፈስ የተነዱ ቅዱሳን ሰዎች የጻፉትን ታሪክ በማጣረዝ በዘመን አበው ማለትም አብርሃም በምድር በሕይወተ ሥጋ እያለ የተሠራውን ሥራ ከ2500 ዓመት ያላነሰ ርቀት ከላቸውና በሐዲስ ኪዳን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት ሆነው የተሾሙትን ሰዎች በሕይወተ ሥጋ ካሉበት ዘመን ጋር በማጣመር ሎጥን ከሰዶም ጥፋት ያወጡትና ሰዶም እንድትቃጠል፡ እሳትን ከሰማይ ያዘነቡት 12ቱ ሐዋርያት ናቸው በማለት አስፍረዋል።

የፈጠራ ታሪኩ እንደሚለው ሐዋርያት ወደ ሎጥ ቤት ገብተው ክርስቶስን እንደሰበኩለትና ሎጥም በጌታ እንዳመነ በዚያ የሚገኙት የሰዶም ሰዎች በሐዋርያት ላይ መከራ እንዳጸኑባቸው በዚህም ምክንያት የሰዶም ሰዎች ወንጌልን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ሐዋርያት ተመልክተው ሀገሪቱን ረግመዋትና የእግራቸውን ትቢያ አራግፈው እንደወጡ ተጽፏል።

እንግዲህ የወደዱትን ማንገሥ ያልወደዱትን መሻር በጊዜው በሥነ ጽሑፋቸው ሥልጣን የነበራቸውና ቤተመቅደሱን የሙጥኝ ይዘው ወንጌልን በመንፈሳዊነት ስም ይሠሩ የነበሩት ጸሐፊዎች እንዲህ ዓይን ያወጣን የታሪክ

ክህደት ያለ ሐፍረት በረከተ ሐዋርያትን ለማግኘት የሚነበብ የሚጸለይ የሚሳለሙት ቅዱስ መጽሐፍ ተብሎ እየተሰበከ በማንም ሳይጠየቁ ዘመን በማስቆጠራቸው በሕዝባችን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ኑሮ ውጥንቅጥ መሆን ዳርገውታል፡፡

( ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ምንባብ ዘሐሙስ )

በቅዱሳን ስም እየተደረገ ያለው ይህ ወንጀል ቤተክርስቲያናችንን ምን ያህል እንደጎዳትና ለዛሬው አለመረጋጋት እንደዳረጋት መገንዘብ ይቻላል ፡፡ አባቶች ይህን የሚያህል ክህደትና ወንጀል የተሸከሙችውን ቤተክርስቲያን ምንም እንከን እንደሌለባት በማስመሰል ለእርምት ከመነሣት ይልቅ ሕዝቡ ያለውን ወንጀል ተሸክሞ እንዲቀጥል ያሳዩት ቸልተኝነት የእረኞች አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ አንገታቸውን እንዲደፉ እንደሚያደርጋቸው መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ ወንጀል ይብቃን እግዚአብሔር ሆይ እውነተኞች እንሆን ዘንድ እርዳን፡፡

# የማይቻል ዳዳስ አስከሬን ኃጢአት አስተሰረየ

በቤተክርስቲያናችን የሚገኙትን አገልጋዮች ( ካህናት ) ሕዝቡ ( ምዕመናኑ ) በእግዚአብሔር ምትክ ያያቸዋል የሚባለው ወይም እንደ እግዚአብሔር አምኖ ይቀበላቸዋል እየተባለ የሚነገረው አባባል እውነታው ያመዘነ ነው፡፤ ምክንያቱም ካህናቱ ያሉት ሁሉ ያለተቃውሞ ያለጥርጣሬ አሜን ይሁንልን ይደረግልን በማለት አባቶቹ የአባቶቹም አባቶች ዛሬም እርሱ ራሱ ሕዝቡ እየፈጸመው ያለ ግብር በመሆኑ በቂ ማስረጃ ይሆናል፡፡

ከዚህ የተነሣ ለኃጢአት ሥርየት ያገለግላል የተባለውን ማንኛውም አይነት ነገር አዎ ያስተሰርያል በማለት እየተቀበለ ያንንም እየፈጸመ የሚኖር ከመሆኑም ባሻገር ሰው ይሁን መልአክ እንጨትም ይሁን ድንጋይ ተራራም ይሁን ወንዝ ካህናቱ ኃጢአት ያስተሰርያል ካሉት አዎ ያስተሰርያል ብሎ መቀበል በራሱ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባህልና የአባቶቹ ብሎ የሚኮራበት ታሪክ እየሆነለት ይገኛል፡፡

እንደ ጸሐፊዎቻችን ብዛት ያድናል ያጸድቃል ኃጢአት ያስተሰርያል ይራዳል ከሞት ያድናል ከውርደት ይታደጋል ገበያ ያቀናል፣ ሰላቢ፣ ቡዳ፣

ዓይነጥላ፣ ወዘተ ይከላከላል የተባለውን ሁሉ ይሞክራል። ጠጅሣር ይሁን ጥንጅት፣ ቂጠማ፣ ይሁን ዕጣን፣ የቅጥረ ቤተክርስቲያን አፈር ይሁን የሙጋድ እንጨት፣ አመድ፣ የደመራ አመድ፣ ሆነ ታቦታቱ ያደሩበትን ሜዳ አፈር በየሽለቆው ዛሬ ዛሬ ደግሞ በየአውራ ጎዳናውና በየከተማው የፈነዳ ቧንቧ ሳይቀር ፍሳሹን ተከትለው በተፈበረኩ ውኃዎች ( በአገልጋዮቹ ስያሜ ጠበል ) ጭምር ፊቱን የተቀባ በቤቱ በራፍ ያንጠለጠለ ሰውነቱን ያሻሸ ወዘተ ያለ የሌለ ኃጢአትን ሆነ መከራን ጥርግ ሙልጭ አድርገው ያጠፋሉ እየተባለ ስለሚሰበከው ይኸው የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ ስለሁላችን በደል ሥርዬት ለባሕርይው የማይስማማውን ሞት በመቀበል ወደር የማይገኝለትን ሥርዬት አፍስሶልን በሚገኝበትና በእርሱም ምክንያት ከሚወደድ አባቱ ጋር ታርቀን በምንገኝበት በዚህ በምህረትና በጸጋ ዘመን ይህን መከረኛ ሕዝብ እንደ፣ ባለዛር እንደጠንቋይ፣ እንደሟርተኛ እንደ፣ አስማተኛ እንደ፣ ጋኔን ሳቢ ልማድና ትምህርት ከቅጠል ከውኃ ከአፈር ከአመድ ጋር ደጎንነታችንን በማቆራኘት የአዲሱን ኪዳን ጸጋ ከሕዝባችንና ከሀገራችን ለማባረር ታጥቀው በተነሡ ደላሎች ተጠምዶ ይገኛል።

ውዳሴ ማርያም እየተባለ በሚጠራው መጽሐፍም ምንም እንኳ በውስጡ መልካም የሚመስሉ በርካታ ጽሑፎችን የያዘ መጽሐፍ ቢሆንም ፈጽሞ ከጽሑፉ ጋር ግንኙነት የሌላቸውን አንቀጾች በፈጠራ በመጨመር በጌታ ስም ሽፋን የፈለጉትን መናፍስታዊ አምልኮ ቀላቅለው ሕዝባችንን ሥርየተ ኃጢአቱ መገኛው የካህናቱ ቅርስ አጥንት ( አስከሬን ) ነው በሚል ማሠሪያ የአንዲት ሴትን ሥርዬተ ኃጢአት ታሪክ ይተርካል።

መጽሐፉ የሰኞ ንባብ እያለ ባስቀመጠው ገጽ ከነገሥታት ወገን የሆነች አንዲት ሴት ነበረች በማለት ትረካውን ይጀምራል። ይህች ሴት በዘመኗ ሁሉ የምትሠራውን ኃጢአት እየጻፈችና እየመዘገበች በመዝገብ ታስቀምጥ ነበር ይህን ያደረገችበትም ምክንያት መጽሐፉ እንደሚለው:-

1. ኃጢአቷ ብዙ ስለሆነባት
2. ኃጢአቷንም ለሌላ ሰው መንገር ስላፈረች ነበር ይለናል።

መጽሐፉ ይቀጥልና ይህች ሴት ከዕለታት በአንድ ቀን ዕድሜ ልኳን በወረቀት ያሠፈረችውን ኃጢአቷን ይዛ ቅዱስ ባስልዮስ ወደተባለው ጳጳስ ዘንድ ደረሰች እርሷም ወረቀቱ እንደተጠቀለለ አቡን ሆይ በዚህ ወረቀት የጻፍሁት ኃጢአትሽ ይፋቅልሽ በለኝ አለቺው ጳጳሱም ወዲያው ይፋቅልሽ አሳት ገልጣ

በተመለከተችበት ጊዜም አንዲት ኃጢአት ብቻ ስትቀር ሁሉ ኃጢአቷ ተፍቆላት አገኘችው ::

ሴቲቱም ይህች የቀረችው ኃጢአትስ ብላ ስትጠይቀው ጳጳሱም ይህንስ እኔ የምችለው አይደለም ቅዱስ ኤፍሬም የሚባለው ጳጳስ ነው እንጂ አላት በማለት የሥርዬተ ኃጢአቷን ታሪክ ሊያስተምረን ሞክሯል::

ከየትኛው የሃይማኖት መጽሐፍ እንደተገኘ የትኛው ሐዋርያ እንዳስተማረው ወይስ በየትኛው የቤተክርስቲያን ሥርዓት እንደተገለጠ የሚታወቅ ነገር ባይሆንም በእነ ፊጠራ እንደልቡ ግን ኃጢአት በላኢስ የሚጠፋ እፍ ሲሉት የሚበን አቧራ ፀሐይ ሲመታው እንደሚደርቅ ርጥበት ቀላል ነገር በማድረግ እንበለ ኑዛዜ እንደለ ቃለ ወንጌል እንበለ ክርስቶስ በጳጳሱ የይፋቅልሽ ቃል ከልቧ ሳይሆን በወረቀት ላይ የነበረ የኃጢአት ዝርዝር ሙልጭ ብሎ ተሰርዮላት በሙላት ለኃጢአት ሥርዬት የፈሰሰውን ክቡር የክርስቶስ ደም ከንቱ በማድረግ የሰጡ ሰዎች እንደሆኑ መረዳት አያዳግትም::

## ለከፍተኛ የኃጢአት ሥርዬት
## ወደ አባ ኤፍሬም

አባ ባስልዮስ በተባሉት ጳጳስ ሳይቻል ቀርቶ አንዲት ኃጢአት በመዝገቧላይ የቀረባት ሴት ለከፍተኛ ሥርዬት አባ ኤፍሬም ይባላሉ ወደተባሉ ሰው እንድትሄድ ትዕዛዝ የተቀበለችው ሴት ቀርቷል የተባለችውን ኃጢአት በያዘችው ወረቅት እንዳለ በመሄድ አባ ኤፍሬም ከተባሉት ሰው ፊት ደርሳ እንደተለመደው አባ ይፋቅልሽ በለኝ በማለት ስትናገር ጳጳሱም ይህስ ኃጢአት ለእኔ አይቻለኝም ለቅዱስ ባስልዮስ ነው እንጂ በማለት እንድትመላለስ ተናገራት:: ያንጊዜ ሴቲቱ ወደተጠቆማት ሰው ልትሄድ ፊቷን ስታቀና አባ ኤፍሬም እንዲህ አላት አሁን ስትመለሺ አባ ባስልዮስን እንደቀድሞው በሕይወተ ሥጋ አታገኚውም ነገር ግን ሳትጠራጠሪ የያዝሽውን ወረቀት በአስከሬኑ ላይ ጣይው ያን ጊዜ የቀረው ኃጢአትሽ ይፋቅልሻል አላት ይላል ::

ሴቲቱም ስትሄድ አስቀድሞ ለከፍተኛ ሥርዬት ልኳት የነበረው ሰው ( አባ ባስልዮስ ) ሞቶ ሊቀብሩት ሲሄዱ መንገድ ላይ አገኘችው እርሷም እንደተባለችው በእጇ የያዘችውን ወረቀት ( ኃጢአቷ ያለበትን ) አስከሬኑ ላይ ስትጥለው ቀርታ የነበረችው ኃጢአቷ ተፍቆላት እንደተመለሰች የሚተርከውን ተረት ያገባድዳል ::

እንዴት ያለ ቀልድ እንዴት ያለ ወንጀል በቤተክርስቲያንና በሕዝቡ ላይ በቅዱሳን ስም ይፈጸም እንደነበር በክርስቶስ አምናለሁ የሚል ክርስቲያን በቀላሉ ሊረዳው ይችላል እንላለን:: ጸሐፊው በሴትዮዋ ላይ የተደረገውን ትያትር ምክንያት ሲያስረዳ ወደ ከፍተኛ ሥርዬተ ኃጢአት የተላከችበት ምክንያት :-

2. ቅዱሳን የራሳቸው ክብር እንዲገለጥ ሳይሆን የጓደኞቻቸው ጽድቅ እንዲገለጥ ስለሚወዱ ነው
3. ሴቲቱ ወዲያና ወዲህ ስትመላለስ ድካሟ ንስሐ እንዲሆንላት ነው ይለናል::
4. ይህም ታሪክ የሚያስረዳን ይላል መጽሐፉ ካህናት በሕይወት እያሉ ብቻ ሳይሆን ከሞቱም በኋላ ኃጢአትን ማስተስርይ እንደሚችሉ ለማስረዳት ነው ይላል::

ይህን የፈጠራ የኃጢአት ማስተስረያ መንገድ በመጽሐፍ ቅዱስ ስንመዝነው መጽሐፋችን ወንጀልና ድብቅ ሤራ ቁልጭ አድርጎልናል::

**የኃጢአት ሥርዬት በመጽሐፍ ቅዱስ**

አስቀድሞ ሁላችንም በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአተኞች በመሆናችን ከእግዚአብሔር ጋር የነበረን ግንኙነትና ኅብረት ተበላሽቶ ነበር (        ) ማንም ደግሞ ይህን የተበላሸ ኅብርት ለማስተካከል በራሱ ባለመቻሉ እግዚአብሐር ራሱ የሚበጀንን የምህረት ኪዳን በፍጡር ሰው ወይም በመላእክት ሳይሆን በባሕሪይ በመልክ በሚተካከለው አንድያ ልጁ በኩል በሥጋ ተዛምዶን ስለሁላችን በደል ተወክሉ በሥጋው በመቀጣት ( በመሞት ) በእርሱ ሞት ምክንያት ከእርሱ ከአባቱና ከመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ጋር ታረቅን አስታረቀን::

ስለሆነም የመጀመሪያው ሥርዬተ ኃጢአት የማንም ፍጡር ሰውና መልአክ እጅ ሳይኖርበት ወይም ሳይገባበት በራሱ በእግዚአብሔርነቱ ፈቃድና ውሳኔ ተፈጸመልን :: እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር በደላቸውንም አይቆጥርባቸውም ነበር ( 2ቆሮ5÷19 ) እንደተባለው ነው::

ይህን በራሱ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተፈጸመ ሥርዬተ ኃጢአት ለመቀበል እግዚአብሔር የላከውን ልጁን ማወቅ ማመንና መቀበል ይገባዋል ( ዮሐ1:12 ) ምንም እንኳ ከእግዚአብሔር ለይቶን የነበረውን የጥል ግድግዳ ( ኃጢአት ) ሥርዬት በእርሱ ውሳኔና ፍርድ እንዲህ ሳንደክም በጸጋው በኩል

የተቀበልን የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን የተጠራን ነን ብንልም በኃጢአትና ከሥጋ ጋር የምንኖር ስለሆንን በዕለት ተዕለት ተግባራችን ላይ ሕይወታችን ከስሕተት ሊያመልጥ ባለመቻሉ እግዚአብሔር ቀሪ በሥጋ ልንኖርባት የተሰጠንን ዕድሜ እንዴት ተጠንቅቀን እንደምንኖር መፍትሔውን ጭምር ሠርቶልናል። በዕለት ተዕለት በሚከናወነው ኑሮአችን ላይ የሚፈጸም የገቢርና የኃልዮ ኃጢአት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት ስለሚያበላሽ ( 1ኛ ዮሐ 1:3 ) ይህን ኃጢአት የሚያበላሸውን ኅብረት በየጊዜው ለማስተካከል ወይም ለማደስ መፍቴው በሠራነው ኃጢአት በመጸጸት በእግዚአብሔር ፊት መናዘዝ ብቻ እንደሆነ ተገልጾልናል።

« በእውነት ብንናዘዝ ከኃጢአታችን ሁሉ ከአመጻም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው » በማለት ገልጦ እርሱም ክርስቶስ ነው ይለናል። ስለ ሥርዬተ ኃጢአቱ አፈጻጸም ሲያስረዳ « ልጆቼ ሆይ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ ማንም ኃጢአት ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ክርስቶስ ነው » (1ዮሐ2:1) ካለ በኋላ የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻል ( 1ዮሐ1:9 ) ብሎ ኃጢአትን ለማስተስረይም በአብ ፈቃድ የተሾመልን ሊቀ ካህናት እርሱ ብቻ እንደሆነ ሲያስረዳ « በብሉይ ኪዳን ኃጢአትን ሊያስተሰርዩ የቆሙ ካህናት ብዙ ናቸው እነርሱ ግን ሞት ስለከለከላቸው ካህናት እየተባሉ የተሾሙ ብዙ ናቸው እርሱ ግን ለዘላለም ስለሚኖር የማይለወጥ ክህነት አለው ብሎ ስለዚህ ለእነርሱ ሊያማልድ ( ሊታይ ሊከራከር ይችላል ይሉታል የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ) በሀይወት ይኖራል ስለዚህ በእርሱ በኩል የሚቀርቡትን ፈጽሞ ሊያድን ይችላል በማለት የኃጢአት ሥርዬት ሁኔታን ያስረዳናል።

በሌላም ሥፍራ የሚያስፈልገን ሊቀ ካህናት እንዲህ ያለው ነው በማለት ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር ይሁንላችሁ ብሎ ወደ ሾመልን ሊቀ ካህናት እየቀረበ የበደሉን ሥርዬት እንዲቀበል ሐዋርያት ይመክሩናል፡ የውዳሴ ማርያምን መጽሐፍ ጽፈነዋል ያሉትን ኢትዮጵያውያን መናፍቃን ግን የኃጢአት ሥርዬት ለማግኘት በሟች ሰው አስከሬን ላይ ኃጢአትን ጽፎ በመጣል ነው በማለት ለዚህ ሥራ ያስቀመጣቸው ካህናት ናቸውና በህይወታቸውም በሞታቸውም ቢሆን ኃጢአትን ማስፋቅ ይችላሉ በማለት ታሪክ ቧልቱን ለቅልቆልናል።

ሌላው ተራራ በመውጣትና በመውረድ በሚፈጠር ድካም ንሥሐና ሥርዬተ ኃጢአት ይገኛል በማለት በድፍረት በጌታ ደም ላይ የተነሳሱ ሰዎች በመጻፋቸው ጽድቅ ፍለጋ ከገዳም ገዳም ከደብር ደብር እየተንከራተቱ ላቡን ጠፍ እያደረገ በአካሉና በሕይወቱ ላይ አደጋን የፈጠሩ ሰዎቻችን ቀላል አይደሉም ይህም ጉዳት የጽድቅ ምልክት ሆኖ እንዳገለገላቸው ስለሚሰበክ ከክርስቶስ ደም ይልቅ የመናፍቃኑ ትምህርት አይሎ ዛሬም እንኳ ይኸው ትምህርት ቤተክርስቲያኒቱን ገዝቶ ይዟት ይገኛል።

የእግዚአብሔር ልጅ በፈቃዱ ከዙፋኑ ፍቅር አስገድዶት ለሞት ያውም ለመስቀል ሞት ራሱን ሰጥቶ በከበረች ሞቱና ደም ማፍሰሱ ጽድቅ ቅድስና ቤዛነት ሥርዬተ ኃጢአት ተሰብኮልን እግዚአብሔር አብም አንድያ ልጁን በመስጠት የገለጠውን ፍቅር ከንቱ ለማድረግ በተደረገ የመናፍቃን ሤራ የሚች አስከሬን የኃጢአት ሥርየትን ይሰጣል ብሎ መስበክ የእግዚአብሔርን ጸጋ ማክፋፋት አይሆንምን ?

# ጽንስ በምራቅ እናስተላልፋለን

**ዑራኤል**

ልመናውና አማላጅነቱ ለዘለዓለሙ በእውነት ከወዳጁ ጋር ይሁንና የመላእክት አለቃ ቅዱስ ዑራኤል ያደረገው ተአምር ይህ ነው።

ከምዕራብ ወይም ከዓረብ አገር የመጣች አንዲት ሴት ነበረች፡ ይህችም ሴት ልጅ የሌላት መካን ነበረች። ይህም የወራት ግዳጁ በየጊዜው እያስጨነቃት እንደጎርፍ እየወረደ ሰውነቷን ያደክማት ነበር። ከዕለታት በአንደኛው ቀን ወደ ቅዱስ ዑራኤል ቤተክርስቲያን ዘንድ ሄዳ ብዙ በማልቀስ ልትጸልይ ከዐፀደ ቤተክርስቲያን በስተውጪ ስትጸልይና ስታለቅስ ብዙ ጊዜ ቆየች።

ይህቺ ሴት ከቤተ-ክርስቲያኑ ውጭ በሆነ በዐፀዱ ውስጥ ቆማ ብዙ ጊዜ መዘግየቷን ቀሳውስቱና ዲያቆናቱ ባዩ ጊዜ አንቺ ሴትዮ ሥራሽ ምንድን ነው? ምንስ ትፈልጊያቀሽ ? ሲሉ ጠየቋት። እርሷም ልጅ እንደሌላትና ለብዙ ዘመን መካን ሆና ስታለቅስ ስታዝንና ስትተክዝ የኖረች መሆኗን ነገረቻቸው።

ያን ጊዜ ወደ ቅዱስ ዑራኤል ስለት ተሳይ እርሱም መልካም ልጅ ይሰጥሻል አሏት:: እርሷም እንደቃላችሁ አደርጋለሁ አለቻቸው:: እስከ ዛሬ ዓመት ድረስ ማኅፀኔን ልጅ ለመውለድ የከፈተ ልኝ እንደሆነ እስከ ዕለተ ሞቴ አገለግለ ዋለሁ በማለት ወደ አገሯ ተመለሰች::

በመንገድም ስትሄድ የምታውቃት አንዲት ሴት አገኘችና ሰላም አለቻት ከጥንት ጀምሮ ስለምታውቃትም ሁለቱ አፍ ለአፍ ገጥመው ተሳሳሙ ያንጊዜ በመንገድ ያገኘቻት ሴትዮ የፀነሰች ስለነበረች በሚሳ ሳሙበት ጊዜ የፀነሰችው ሴት ምራቅ ባልፀነሰችው ሴት አፍ ገባና ከወንድ ሳትገናኝ በዚያው ብቻ ፀነሰች::

በዚህ ጊዜ የወር ግዳጇ ቆመና ቅሪት ሆና ወይም ፀንሳ በፍጹም ደስታ ወደ ቤት ገባች:: ከሦስት ወር በኋላ ጎረቤቶቿ ከምክንትሽ እንዴት ዳንሽ እንዴትስ ስለሰማሽ ነው የተወደደ ልጅ የሰጠሽ? አሏት::

ከሰባት ወር በኋላም ልጅ ወለደችና በክንዷ ታቅፋ እግዚአብሔርን አመሰገነች ስለ እምነቷም የተወደደ ልጅን አገኘች :: ወልዳ ሦስት ወር ከሆናት በኋላ ወደ ቅዱስ ዑራኤል ቤተ-ክርስቲያን ዘንድ ሄደችና የከበሩ ልብሶቿን የወርቅ ጌጣ ጌጧን ሌላም ሌላም ብዙ መባን ሰጠች::
ቀሳውስቱ ንና ዲያቆናቱንም አመሰገ ነቻቸው::

እንዲሁም ተአምር ሠሪ በሆነ በቅዱስ ዑራኤል አማላጅነት ልጅን ስለሰጣት እግዚአብሔርን አመሰገነች:: ከዚያም ዕለት ጀምራ እስከ ዕለተ ሞቷ በመልካም አገልግሎት ቤተ-ክርቲያኗን ስታገለግል ኖረች::
የመላእክት አለቃ የሚሆን የቅዱስ ዑራኤል ልመናውና በረከቱ ለዘለዓለሙ ከወዳጁ ጋር ይሁን አሜን::
(ድርሳነ ዑራኤል ዘየካቲት 5ኛ ተአምር )

## ተአምር ይኋል እንዲህ ነው

እግዚአብሔር ተአምር ሠሪ አምላክ መሆኑን ሰማይና ምድር በውስጣቸው ያሉ ፍጥረታትም ሳይቀሩ አሜን የሚሉት እውነት ነው መዝሙረኛው ዳዊት እንዳለ «ያለ ቃል ያለፊደል አሜንታቸውን እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ያሰማሉ» /መዝ19:1/ በእውነትም አምላካችን ከአዕምሮ በላይ የሆነ ተአምር ይሠራል:: ለሰው የማይቻል ሁሉ ለእግዚአብሔር ይቻላል የሚለው ቃል እውነት ነውና::

መልአከ ብሥራት የሆነው ቅዱስ ገብርኤል ለድንግል ማርያም ሲናገራት ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና /ሉቃ1:37/ አለ:: ራሱ እግዚአብሔር በወዳጁ በአብርሃም ቤት በገባ ጊዜ የአብርሃም ሚስት ሣራ ልጅ የመውለዷ ነገር በእግዚአብሔር አፍ ሲነገር ስምታ ዕርጅናዋ ይህን የእግዚአብሔር ተአምር ለመቀበል ሲያግዳት በሳቀች ጊዜ በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን ብሏታል:: /ዘፍ18:13/

ጌታችንም በመዋዕለ ስብከቱ ሲናገር ለሰው የማይቻለው ለእግዚአብሔር ይቻለዋል ብሏል:: /ማቴ19:26/ ስለሆነም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ከምንለው በላይ ተአምር ይሠራል:: እንደሚሠራው በነፍሳችን ተወራርደን የቆምንበት ዓላማችን ነው:: አዎ ልዑል እግዚአብሔር ተአምረኛ አምላክ ነው::

ይሁንና «እስመ አልቦ ነገር» የምትለውን ሐረግ ስቦ ለክፋትና ለአመፅ እንዲሁም ለሰይጣን ግብር መሸፈኛ ማድረግ ግን እምቢ ልንለው የሚገባ ትምህርት እንደሆነ እንገልጻለን::

አተካከሏ በእውነት ወንጌል በደጋግ መምህራን እንደነበር የሚነገርላት ቤተ-ክርስቲያናችን ዘመንና የጠላት ሰይጣን ዕቅድ ያስለጠናቸው ክፉዎች ከላይ እንደገለጥነው «እስመ አልቦ ነገር ዘይሰአኖ ለእግዚአብሔር» በሚለው ሽፋን ባዕድ ትምህርት ባዕድ ባሕልና ሥርዓት ወደ ቤተ-መቅደስ በማስገባታቸው ከጨለማው ዘመን ጀምሮ እስከዛሬ ያልተነቀለ አሳፋሪ አስነዋሪ ወንጀሎች በቤተ-ክርስቲያናችን ስም ተለጥፈው ለዛሬ አንገት መድፋት ምክንያቶቻችን ሆነዋል::

ብዙዎችን ያታለለውና ያሳሳተው ነገር ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም የሚለው ጥቅስ ነው:: ነገሩን በመንፈ ሳዊነት በቃለ እግዚአብሔር እውነት ካልመረመርነው ለሀገራችን ምዕመናን ሸክምና ዕዳ ነው::

ብዙ የቤተክርስትያናችን ምዕመናን ሰይጣን እግዚአብሔር ብሎ ለመጥራት የሚፈራ ይመስላቸዋል ስለዚህም እግዚአብሔር ብሎ ከቅድመ አያቶቻችን ከዚያም በፊት ጀምሮ እየተንከባለለ የመጣ የአመፅ ዕዳ ያለ ተቃውሞ ተቀብለው ይኖራሉ::

የሚያሳዝነው ዛሬም እንኳ ለዚህ ጥፋታችን ባለመንቃት ለገጠመን ችግር ምክንያት ሌላ አዳዲስ ነገሮችን እየፈጠርን እነሆ ከእግዚአብሔር ጋር ሳንታረቅ መኖራችን ነው::

ደጋግመን እንደገለጽነው የሀገራችንም ሆነ የቤተ ክርስቲያናችን ችግር መንግሥ ታቶቻችን ድኅነታችን ኋላቀርነታችን የቀለም ትምህርት አለመማራችን

በቴክኒዮሎጂ አለመራቀቃችን ወዘተ አይደለም፡፡ ምናልባት ለብዙ ምሁራን ላይዋጥ ይችላል፡፡ እኛም መሰልጠን በተክኒዎሎጂ ማደግ በቀለም ትምህርት ማደግ ይጎዳል አላልንም አንልምም፡፡

ልንረዳው የሚገባ ግን አንድ ታላቅ ምሥጢር አለ ሀገራችን ወደድንም ጠላንም ከእግዚአብሔር ጋር ያላት ቁርኝት ምሥጢር ነው፡፡

ሀገራችን በቅዱስ መጽሐፍ ታሪክ ውስጥ በቁጣና በበረከት ከተጠቀሱ ሀገራት መካከል አንዷ ነች፡፡ እውነት ነው አባት ልጅን እንዲቀጣ ሀገራችን በእግዚአብሔር በትር የምትቀጣባቸው ምዕራፎች ተገልጠዋል፡፡ ደግሞም ይሆናሉ፡፡ ከተጻፈ ልናመልጥ አይቻለንምና፡፡

ደግሞም የበረከት ምዕራፎች አሉን እነዚህ ምዕራፎች ዓቢይ ዓላማቸው ለእኛ ለሀገራችን ብቻ ሳይሆን ለዓለማችን የሚተርፍ ጸጋና ምህረትን ሊያመጡ የሚችሉ የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው፡፡

በተለይም ኢትዮጵያ ከቅጣት ከግሣጼ በኋላ ወደ እግዚአብሔር በምትቀርብበት ጊዜ የእግዚአብሔር የወንጌል ሠራዊት ከላይኛው የአፍሪካ ክፍል (ግብጽ) ጀምሮ ኑብያን (ሱዳንን) ይዞ የዛሬይቱን ኢትዮጵያንና ላይኛውን ሶማልያ እንዲሁም እስከ የመን ዳር ድረስ ካለው ምድር እንደሚነሣ የታመነ ትንቢት አለን ፡፡

«ይምጽኡ ተናብልት እምግብጽ ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአ ብሔር »አማላጆች(መኳንንቶች) ከግብጽ ይምጡ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአ ብሔር ትዘረጋለች (መዝ 67 /68/ :31) ይላልና አሜን ይሁን ይደረግ ፡፡ ይህን የእግዚአብሔር ተስፋ ኢትዮጵያውያን እንዳያዩ አሊያም እንዳያስተውሉ ሰይጣን በብዙ አይነትና ጎዳና ሰልፍ ከከፈተባቸው ተቆጥሮ የማያልቅ ትውልድ አልፏል ፡፡ጦርነት ረኃብ የእርስ በእርስ ግጭት የቋንቋ የብሔር የጎሣ የነገድ ልዩነቶች እነዚህ የዋናው ኃጢአታችን ቅርንጫፍ ምልክቶች እንጂ በራሳቸው ኃጢአት ሆነው የተገለጡ አይደሉም ፡፡

ብዙዎቻችንም ያልተገለጠልን ነገር ይህ ነው ዛይማኖተኞች የተባሉት እነዚህን ነገሮች ለማጥፋት ዘዴ ሲቀይሱ እምነት አልባ የሆኑት ደግሞም ችግራችን አለማደጋችን አለመማራችን አለመሰልጠናችን ወዘተ ናቸው በማለት ጊዜና ጉልበት ያባክናሉ ፡፡

እስራኤልን ልብ ይሏል እስራኤል በእግዚአብሔር የታሪክ መዝገብ ከፍ ያለውን ሥፍራ ይዛ የምትገኝ ሀገርና ሕዝብ ናት ግና ትዕዛዛቱን ባለመከተል

በአመጸኝነቷ በመግፋቷ ልዑል እንደተናገረ እንደ ምድር አሸዋ በዓለም ሁሉ በተናት ይህን ያደረገባት አለመሠልጠኗ በቴክኖሎጂ አለማደጓ ሳይሆን በእግዚአብሔር ሕግ አለመኖሯ ነው።

እንደተጻፈባትም የተቀጠረላት ቀን እስኪደርስ በዓለም ሁሉ ተበተነች ተሰቃየች እንደተነገረላትም ትሰበሰብ ዘንድ ሰዓቱ ሲደርስ ከተበተኑበት ይሰበሰቡ ዘንድ የዓለም መንግሥታት ዓይናቸው እያዩ ከመንደር ከዓለማት ጥግ ሳይቀር በዘምባባ ዝንጣፊ ሆ እየተባሉ ይሸኛሉ። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን። ዳሩ ልዑል ከተናገረ ማን እምቢ ሲል ፡፡ ኢትዮጵያ በራሱ በእግዚአብሔር አፍ ከእስራኤል እኩል እንዲያውም ከፍ ባለ ንግግር የተጠራች ሀገር ናት ፡፡ ልብ ይሏል ይኸኔ ነው። /መዝ67/68/:31/

ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስና ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በሀገራችን እንዳይገለጥ ሰይጣን ያልከፈለው ዋጋ የለም በጠበብቶች በአጥኝዎች በውጭ ኤክስፐርቶች የተጠኑት ችግሮች ናቸው የተባሉትን በመቅረፍ በመቁረጥ የምንገላገል አይደለም ስልጥነንም በልጽገንም ከእግዚአብሔር ካልታረቅን የሰለጠኑ ስደተኞች የሰለጠኑ መከረኞች የበለጸጉ ባለመከራዎች መሆናችን አይቀሬ ነው።

በጥቅሉ የሀገራችን ችግር እንዳይገለጥ እንዳይወገድም ጋርዶና ሸፍኖ የያዘው ምሥጢር ኮሚኒስትነት ሶሻሊዝምነት ኢምፔሪያሊዝምነት ለዘብተኛነት ዲሞክራትነት ግራ ወይም ቀኝ ክንፍ የፓለቲካ አመለካከት አይደለም።

በዘመኑ የሶሻሊዝምን መመሪያ ወደ አፍሪካ ይዘው በመጡ ጊዜ አፍሪካን በዚህ ሥርዓት ለመሸፈን ከሰለጠኑት ይልቅ አስቸጋሪ እንደሚሆንባቸው ይናገሩ ነበር ምክንያቱም አፍሪካውያን ሁሉ ነገራቸው ሃይማኖተኝነት የተጠናወተው በመሆኑ ሃይማኖት የለም ብለው የኮሚኒዝምን ሐሳብ በሕወታቸው ለማዋሃድ የማይቻል በመሆኑ ነው። ይላሉ።ሆኖም አንዳንድ የሰለጠኑ ሀገሮች የአፍሪካ ችግር ያለመሰልጠን ነው ብለው የሚያስቡም አሉ። ስለሆነም እንሰለጥን ዘንድ እኛ በሌለንበት ስብሰባ ያደርጉልናል ያስቡልናል ብንሰለጥን ከችግራቸው ይላቀቃሉ ብለው። መልካም የሚመስል እውነት ነው፡

አፍሪካውያን ግን ከሥልጣኔው ይልቅ እነሱ እንደሚሉት ዘመናትን ተሻግሮ የመጣን ምንም ይሁን ምን ሃይማኖት ያሉትን ሥርዓትና ትምህርት ያለጥያቄና ያለማጉረምረም አሜን ይሁን እያሉ መኖርን ይመርጣሉ።

ሀገራችንም ተመሳሳይ አቋም ያላት ሀገር ናት:: የኢትዮጵያም ይሁን የአፍሪቃ ችግር ሃይማኖተኝነት ያለ እውቀት መሆኑ ነው:: እውቀት ማለት በሰማይ ለመብረር የሚያበቃው ጥበበ ዓለም ብቻ ማለታችን አይደለም የእምነት እውቀት ማለታችን እንጂ::

ሃይማኖተኝነት ያለ ሃይማኖት እውቀት ሕዝብንም ሀገርንም ያጠፋል «ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቷል» እንደተባለ:: መጽሐፍ እናንተ እውነት ታውቃላችሁ ሲል የሚታወቅ እውነት መኖሩን ሲያስረዳ እውነትም አርነት ያወጣችኋል ሲል ደግሞ ያወቅነው እውቀት የሆነ ነገር /እምነት/ ከማናቸውም መንፈሳዊ ክስረት የተጽዕኖ ነጻነትን ማስጠት የሚያስችል ብቃት ያለው ይሆናል:: ይህም እውነትና ነጻ አውጪ ክርስቶስ ነው::

እምነትና የእምነት እውቀት በአንድነት ካልተገናኙ እናያለን ትላላችሁ ግን አታዩም እንደተባሉት የአይሁድ ካህናት መሆናችን አይቀሬ ነው:: / / አፍሪካ በድኅነቷ እያደገች በመከራ እየበለጸገች እንዲህ የምትታየው የኤቢሲዲ ችግር ብቻውን ሊሆን እንደማይችል አፋችንን ሞልተን እንናገራለን::

ሥልጡናኑ አፍሪካን የሥልጣኔ ችግር ቢኗትም አፍሪካውያን ራሳቸውን በራሳቸው ለማጽናናት ባለቸው ምኞት የሰው ዘር መገኛ፣ ቀደምት ፍጡር፣ የሥልጣኔ አሻራ፣ የድንቅየ አራዊት መኖሪያ በማለት ሲያሞካሹዋት ይገኛሉ።

ለንዲያውም በቅርቡ በቲቪ አፍሪካ ላይ በሚታይ ማስታወቂያ በጠመር የሚደረግ ጥንቆላን የመጀመሪያው የሕክምና መገኛ ምንጭና የሂሳብ ቀመር መነሻ በማለት የአፍሪካን የሃይማኖተኛነት ጉዳይ ተናግረውላታል::

በሃገራችን በኢትዮጵያም ችግራችን መንፈሳዊ ሽፋን ተላብሶ ያደገ በመሆኑ መሪዎቻችንም ሆኑ ጠበብቶቻችን ሊደርሱበት የማይችሉት የተሰወረ ገሃድ የተደበቀ ግልጥ ሆኖባቸው ተቸግረዋል::

365 ቀናት በሚከበሩ በዓላትና ተደግሦ በሚበላበት በሚጠጣበት ሀገር በምግብ ራስን መቻል የሚለው የመንግሥታችን መመሪያ በባሕር ላይ የወደቀ ኩበት አስመስሎታል::

ሕዝባችን መንፈሳዊ የሚመስሉ ቃላቶችን የተናገረ ሁሉ ጻድቅ እየመሰለው በተለይም የሕዝቡን ስህተት እስካልነካ ድረስ ነው የተናጋሪውን ቅድስና ታይቶና ተሰምቶ በማያውቅ ርቀት ከፍ እያደረገ ቅዱስ ዕገሌ የበቁ የነጡ የጠደቁ አዝጌር የሚናገራቸው እመቤቴ የምታነጋግራቸው እያለ በራሱ ላይ ታሥሮ የኖረ ሕዝብ ነው::

አንድ ሰው የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመምራት የሚፈልግ ሁሉ የጦር መሣሪያ ይዞ ከሚዋጋ ይልቅ ጥሩ የሰለጠነ ወሮበላ ባሕታዊ ቢያስማራ ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትገዛ ነበር አሉ ለምን ሲባሉ ለሃይማኖተኛው ሕዝባችን እመቤቴ ተገዙ ብላለች እመቤቴ እንዲህ ብላለች እያለ በመስበክ ሕዝቡን ይይዝለት ነበር በማለት ተናግረዋል::

ነገሩ እውነትነት ያያዘ ትዝብት ነው:: በእርግጥ አባቶቻችን አዝዘዋል ሠለስቱ ምዕት ደንግገዋል እመቤታችን ተገልጣ እንዲህ ብላለች ጻድቁ አባ ዕገሌ ይህን ተናዘው አልፈዋል:: የሚል ጮሌ ሁሉ ከጳጳስ ይልቅ ቦታ ያለው በመሆኑ የሀገራችንን ችግር ውል ውስብስብ እንዲል አድርጎታል::

ሃይማኖተኝነታችን በበጎ ጎኑ ሊታይ የሚችለው የዘላለምን አምላክ እግዚአብ ሔርን የዘላለም አምላክ ስንሰብከውና ስናስከብረው ብቻ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ እንደሚ ያስረዳን የዚህ ዓለም ሰዎች የእግዚ አብሔር ቁጣ በላያቸው ላይ የሆነበትን ምክንያት ሲናገር እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ ስላላከበሩት ነው ይለናል /ሮሜ1÷21/ እነዚህ ሰዎች ሃይማኖተኞች ናቸው የሚጠሩትም እግዚአብሔርን ነው ነገር ግን እንደ እግዚአብሔርነቱ አይደለም ይህም ማለት እግዚአብሔር እንዲመለክ እንዲመሰገን የሚገባው ከሰው በወጣ መስፈርትና ፍላጎት ላይ በተመሠረተ መመሪያ ሳይሆን ሊመሰገንበት በሚሻው መንገድና ሁኔታ እንዲከበር ባለሥልጣኑ እርሱ ሆኖ እያለ እንደመሰላቸው ወይም ይህም መልካም ነው ያም መልካም ነው በሚል ሰውኛ አሳቤ ሊያመልኩት የሚወዱ ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ እንደማያመልጡ ሲናጋር እንደ እግዚአብሔርነቱ ስላላከበሩት አለ::

ሕዝባችን እግዚአብሔርን የሚፈራ የሚወድ እየተባለ ረጅም ዘመን ተነግሮ ለታል ይመስላልም ይሁን እንጂ እግዚአ ብሔርን መፍራት ለእግዚአብሔር መታዘዙ ዕገሌ እንዳለው ዕገሊት እንዳላቸው በሚል የተንኮለኞች ፈሊጥ የተሞላ በመ ሆኑ በልቡ የራቀ በከንፈሩ የሚያመልክ ሆኗል::

ይህ የተሸፈነ መንፈሳዊነት ምንም ነገር ቀና ብሎ ለማየት ዕድል ስለማይሰጠው በሕይወቱ ላይ የተደገሰውን የጠላት እቅድ ያለተቃውሞ ሲያስተናግደው ኖሯል::

«ለሰው ልጆች ሲል በመስቀል ላይ የተሰቀለ የእሾህ አክሊልን በራሱ የደፋ መርቆሬዎስ ነው» ብለው ሲያዜሙለት አሜን ከማለት ውጪ አማራጭ የሌለው ሕዝባችን ክፉዎች ካስተማሩትና ካስለመዱት የተንኮል ትምህርት መላቀቅ የሞት ያህል ሆኖበት ዛሬም እንኳ ዕድሜውን በዚያው እንዲያሳልፍ ሆኗል።

በዚህ ድርሳነ ዑራኤል በተባለ መጽሐፍ እንዲህ የሚል ክህደት ይገኛል። ልቡን በክፉዎች ትምህርት የተነጠቀው ሕዝ ባችን ይህንና ይህን መሰል በሃይማኖት ሽፋን የተሰበደ ወንጀል እየተፈጸበት ሳይ ረዳ ቆይቷል።

## ጽሑፉ ሲመዘን

## 1 ጽንስን የሚሰጥ ማን ነው ?

መጽሐፍ ቅዱስ የማኅፀን ዘጊና ከፋች እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ይናገራል ።/ኢሳ 66:9/ የእግዚአብሔር ሰው የያዕቆብ ሚስት ራሔል መካን ሆና ልጅን መውለድ ባልቻለች ጊዜ ባልዋን ያዕቆብን «ልጅ ስጠኝ ይህስ ካልሆነ እሞታለሁ » ብላው ነበር። እርሱም እንደ ዛሬዎቹ በቤተ ክርስቲያናችን እንዳሉት መናፍቃን «ዑራኤል ይስጥሽ» አልያም »ዑራኤልን ስለት በመስጠት እንለምን አላላትም » ማኅፀንን የሚከፍትና የሚዘጋ ማን እንደሆነ ስለሚያውቅ «በውኑ እኔ የሆድሽን ፍሬ በነሳሽ በእግዚአብሔር ቦታ ነኝን »? አላት (ዘፍ 30:2)

እንዲሁም በእግዚአብሔር ፊት በሞገስና በጥበብ በማደግ ለእስራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር ፊት ይቆም ዘንድ የተሾመውን ሳሙኤልን የወለደች እናቱ ሐና መካን ነበረች ። መጽሐፍ ስለ ሐና ሲናገር «እግዚአብሔር ማኅፀኗን ዘግቶ ነበር »ይላል (1ሳሙ 1÷6) ሐና ራሷ የማኅፀን ዘጊና ከፋች ማን እንደሆነ የተረዳች ሴት ስለነበረች«ሁል ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ትጸልይ ነበር » ተብላለች። (1ኛሳሙ1:10) ሐና ጸሎቷ ያልገባቸው የጊዜው ካህናት ሰክረሻል ቢሏትም እርሷ ግን ልጅን ወደሚሰጥ አምላክ ወደ እግዚአብሔር ትጮህ ነበር ፡

ወደ ልቡ የተመለሰው የወቅቱ ሊቀ ካህናት ዔሊ እንደዛሬዎቹ በድርሳነ ዑራኤል ላይ እንደተገለጡት ካህናትና ዲያቆናት « ለቅዱስ ዑራኤል ስለትን ተሳይ ልጅም ይሰጥሻል » ሳይሆን « የእስራኤል አምላክ የለመንሽውን ይስጥሽ » ነበር ያላት ( 1ኛ ሳሙ 1÷ 17 )

ሐናም ፀነሰች በወለደችም ጊዜ «ከእግዚአብሔር ለምኘዋለሁና ስትል ስሙን ሳሙኤል አለችው » ተባለ ( 1ኛ ሳሙ 1÷ 20 ) እነ መፍቀሬ ድርሳን ወገድል ግን ከዑራኤል ለምኘዋለሁና « ገብረ ዑራኤል ፤ ወለተ ዑራኤል ወዘተ » እያሉ ሰውን የሚያህል ክቡር ፍጡር ለማይታወቅ አምላክ አሳልፈው ይሰጡታል።

በአዲስ ኪዳን መግቢያ (መሸጋገሪያ) ላይ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ሰሞነኛ የነበረው የካህኑ የዘካርያስ ሚስት ኤልሳቤጥ መካን በነበረችበት ጊዜ ካህኑና ሚስቱ በእግዚአብሔር ፊት የነበራቸው ጸሎት መሰማቱን መልአኩ ተገልጦ ሲነግረው « ጸሎትህ በእግዚአብሔር ፊት ተሰምቶልሃል » አለው ( ሉቃ 1÷ 13 ) ዘካርያስ ይጸልይ የነበረው ወደ ዑራኤል ነው ? ወይስ ወደ እግዚአብሔር? የዘካርያስ ጸሎት አድርሻ ወደ እግዚአብሔር መሆኑን የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤል አመጣጥ በግልጽ ያሳየናል፡ « እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆም ገብርኤል ነኝ » ከማለቱም ባሻገር « ከእግዚአብሔር ተልኮ » ተብሏል ( ሉቃ 1÷ 27 )

ኤልሳቤጥ በወለደች ጊዜ እንደድርሳነ ዑራኤል ሰባኪዎች ስለታቸውን ለዑራኤል ሲሰጡና ደግሰው ሲያበሉ አልታየም እንዲያውም ወንጌላዊው ሉቃስ በምዕ2÷ 57 - 59 ላይ በኤልሳቤጥ መጽነስ ጎረቤት ተሰበሰበ ምክንያቱንም ሲያስረዳን « ጌታ ምሕረቱን ስላገነነላት፡ነው» በማለት ግልጥ አድርጎልናል።

ሐና መካንነቷን ባነሳላት በእግዚአብሔር ተደስታ ስትዘምር እንደዛሬዎቹ መናፍቃን « ምስጋና ለዑራኤል » ሳይሆን ያለችው « ልቤ በእግዚአብሔር ጸና ቀንዴ በእግዚአብሔር ከፍ ከፍ አለ » አለች እንጂ ( 1ኛ ሳሙ 2÷1 - 2 )

## 3. ጽንስ በምራቅ ይተላለፋልን?

ድርሳነ ዑራኤል ስለፈጠረው ምትሐቱ ከተደናቂ የልብ ወለድ ድርሰት ክፍል ሊመደብለት ይችላል ። ሆኖም ከሕዝባችንና ከቤተክርስያናችን ትከሻ ላይ አሽቀንጥረን የምንጥለው እንዲህ አይነቱ የተረት መጽሐፍ ጎራውን ወደ ልብ ወለድ መጻሕፍት እንዲያደርግ እንመክራለን።

እግዚአብሔር በፍጥረት ሕግ ምድር እንድትሸፈንና እንድትሞላ ሲደነግግ ለሌሎች ፍጥታት « ሁሉ እንደወገኑ እንዲያፈራ » አዝዞ ስለ ሰው ሲናገር « ሴትና ወንድ አድርጎ ፈጠራቸው ብዙ ተባዙ ምድርንም

ሙሉአት » በማለት የመባዣ መንገዳቸው የሁለቱ ጾታ ኅብረት እንደሆነ አስረድቷል፡፡

ያለ አባትና ያለ እናት በእግዚአብሔር የማስገኘት ሥልጣንና ትዕዛዝ የተገኙ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች አዳምና ሔዋን ሲሆኑ በኋለኛው ዘመን ሰውን ለማዳን በወደደ ጊዜ ከሦስቱ አካላት አንዱ የሆነውን ወልድን የባሕርይ አባቱ አብ ወደዚህ ዓለም ሲልከው በጥንተ ልደት ያለ እናት ኋላም ያለ አባት በሥጋ ልደት የተገኘው እርሱ ክርስቶስ ብቻ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

በሳይንሱም ዓለም በብልቃጥም በላብራቶሪ የሰውን ዘር ሆነ የእንስሳትን ዘር ለማባዛት ባደረጉት ኢክርስቲያናዊ ፍልስፍናቸው እንኳ ያለሴትና ያለወንድ ዘር ጥምረት ልጅ እንደማይገኝ ሊክዱ አልተቻላቸውም፡፡

እንደ ድርሳነ ዑራኤል ተረት ጸሐፊ ግን መካኗ ሴት የፀነሰችን ሴት በመንገድ ባገኘቻት ጊዜ በዑራኤል ልዩ ችሎታ አፍ ለአፍ በተሳሳሙ ጊዜ የጸነሰችው ሴት ምራቅ ወደ አልፀነሰችው ሴት ሰውነት በመተላለፉ እንበለ ዘርዓ ብእሲ ( ያለ ወንድ ዘር ) በሴቲቱ ምራቅ ልጅን ፀነሰች በማለት የእግዚአብሔርን የፍጥረት ሕግ በመጣስ ሕዝቡን አመጸኝነት ያስተምራሉ፡፡

አንባብያን ሆይ ክፉዎች ለምን ይህን ያህል ለክፉ ነገር እንደደከሙ ልናጤነው ይገባል ፡፡ ሕዝባችን በእንዲህ ዓይነቱ የክፉዎች ተንኮል እስከመቼስ ሊታሠር ይችላል ? ወግድ የክህደት አባትና ፈጣሪ ብሎ ሊጥለው ይገባል፡፡

ሐና በእግዚአብሔር ፊት ስለመካንነቷ በጸለየች ጊዜ ፅንሱን የሰጣት እግዚአብሔር እንኳ እንደዑራኤል አጋፋሪዎቹ ስብከት በነፋስ ወይም ያለ ወንድ ዘር ልጅን እንድታገኝ አላለም ወይም በተአምር ፀነሰች አላለም « ሕልቃናም ሚስቱን (ሐናን) አወቃት» ብሎ እግዚአብሔርም አሰባት ይላል፡፡ ( 1ኛ ሳሙ 1÷ 19 )

ሰውነታቸው እንደሙት የተቆጠረው የአብርሃምና የሣራ እንኳ ልጅን በራሱ በእግዚአብሔር አንደበት እንደሚያገኙ ሲነገራቸው ስላረጀህ በነፋስ፣ በምራቅ፣ በላብ፣ ወዘተ ሳይሆን አብርሃም ሣራን በማወቅ ነበር ( ዘፍ 21 )

3. ከንፈር ለከንፈር መሳሳም

በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት መሠረት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ « በተቀደሰ አሳሳም ተሳሳሙ » ያለውን በጥንቃቄ ተመልክታ ለዝሙት

/ሰፈቲው/ በማያነሣሣ ለፈተና በማይዳርግ መልኩ ትከሻዎችን በመሳሳም ( የአንዱ ሰው አፍ የሌላውን ትከሻ በመሳም ) ያደረገቸውን ሕግ በመጣስ ይልቁንም ልቅ የሆነውን የወሲብ ፍላጎታቸውን ዓለም ሁሉ እንዲያውቅላቸውና ዓለሙም በዚህ የጥፋት ጎዳና እንዲከተላቸው በፊልሞችና በስዕላት ላይ እየቀረጹ ለዓለም እንደሚያዳርሱ መፍቀርያነ ዝሙት መንፈሳዊ ሽፋን ተሰጥቶት ያውም ሴትና ሴት ከንፈር ለከንፈር ሲሳሳሙ ዑራኤል ደስ ብሎት ልጅ እስከ መስጠት ያደረሰበትን ታሪክ አይተናል።

ክርስትና የሌላቸው ሰዎች እንኳ በአምሳለ እግዚአብሔር ተፈጥረዋልና ባለቻቸው ቅን ሰብአዊ አዕምሮ እንዲህ ዓይነቱ ዝሙታዊ ግብር ትውልዱን እንዳበላሸው በመመልከት ቪዲዮ ቤቶች እንዲዘጉ አንጉል የወጣቶችን የወሲብ ፍላጎት የሚቀሰቅሱ ጽሑፎች እንዳይሰራጩ ለመከልከል በሚነጋገሩበት በዚህ ዘመን ዑራኤልና የዑራኤል ወዳጆች ነን ባዮች ግን በቤተ መቅደስ ያውም ሴትና ሴት ከንፈር ለከንፈር ገጥመው ሰላምታ አይሉት ... የዑራኤል ድርሳን ብሎ ሰው እንዲሳለመውና እንዲያነበው ከግዝትና ከቃል ኪዳን ጋር ማድረጋቸው ሰይጣን ምን ያህል በቤተመቅደስ ቦታ መያዙን ያሳየናል ::

እንግዲያውስ እንንቃ አንድ አምላክ አለን እርሱም ከዘላለም እስከ ዘላላም የሚኖር የሁሉ ነገር መገኛ ዘሀሎ ወይሄሉ ( ያለና የሚኖር ) በሦስትነቱ ያለ አምላክ አለን። እርሱ ይገድላል ያድናልም ይሽራል ይሾማልም ያከብራል ያዋርዳልም ይሰጣል ይነሳልም ሁሉ በእጁ ሁሉ በሥልጣኑ ሥር ነው መስጠትም መንሳትም የእርሱ ብቻ ናቸው አሜን።

ታዲያ የድርሳነ ዑራኤል ዓላማ ምን ይሆን ?

1. በመንፈሳዊ ሽፋን በሚደረግ ኃጢአት ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ማራቅ
2. የእግዚአብሔርን ክብር ከፋዎች ለፈጠሯቸው ባዕዳን አማልክት መስጠትና እግዚአብሔርን ከሕዝቡ ልብ ማውጣት
3. ዝሙታዊ ግብርን መንፈሳዊ ሽፋን መስጠት
4. የሰይጣንን ሥራ በውክልና መሥራት ናቸው።

ማሳሰቢያ:-

በብዙ ጋዜጦቻችን እንደገለጥነው እኛ የከፋዎችን ሥራ መልሰን ለመጻፍ ፈልገን ሳይሆን ያለ እውቀት በየዋህነት እየተነዳላቸው ያለው ሕዝባችን ስለሚሠራበት ነገር እውቀት አግኝቶ እውነቱን እውነት ሐሰቱን ሐሰት ብሎ

ክርስቶስን በማወቅና በማመን መዳን ወደ ሚገኝበት ዕውቀትና ጥበብ ወደ ሆነው ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲመጣ ለማገዝ ብቻ ነው።

አንዳንዶች እንደሚሉትም ሰድቦ ለሰዳቢ ለመስጠት የተደበቀ ምሥጢር ለማውጣት በእውነተኞቹ ቅዱሳን መላእክትና ጻድቃን ለመቀለድ አይደለም ይልቁንም የቤተ ክርስቲያናችንን ክብር ለመጠበቅ ዘብ የቆምን ቤተክርስቲያናችንን የሚያዋርር ዷትንም ከሥፍራቸው ለመንቀል ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሠራ ባሪያዎቹ ነን

ሎቱ ለባሕቲቱ ይደሉ ክብር ወስብሐት ለእርሱ ለብቻው ክብርና ምሥጋና ይገባል። አሜን።